# ታ ር ካ ብ

ከትዝብት ማሕደር



## ብዙአየሁ አበጀ

መጋቢት, 2005 ዓ/ም
March 2013

ስለ መጽሐፉ አስተያየት ወይም ለማሰራጨት ጥያቄ ቢኖርዎ አድራሻችን:
Bizuayehu Abeje
2414 CENTAURUS DR
GARLAND, TEXAS 75044
ስልክ፡972-372-9703
Email: Bizu@bestethiobooks.com

## ምስጋና

ይህችን "ታርካብ" ከትዝብት ማሕደር" የተባለች መለስተኛ መጽሐፍ ከሃሳብ ዕመቃ ወደ ጠቃሚ ዕቃ እንድትደርስ ድጋፉን ላለየኝ ቸር እግዚአብሔር ምስጋና ይሁንልኝ።

## መታሰቢያነቱ

ከመቸውም ጊዜ የበለጠ የጀመርሁትን ሥራ እንድጨርስ ምክንያት ለሆኑኝ ለባለቤቴ ለወ/ሮ ሂሩት ኃይሉ ለልጆቼ በዕምነት ብዙአየሁ እና ምህረት ብዙአየሁ ይሁንልኝ።





## የትረካ ርዕሶች | ገፅ


- ጉንጭ አልፋ 7
- ከአንዱም ሳትሆን ቀረች 12
- ደከመኝ አላልኩም 17
- ስልጣኔ የበላው ባሕል 17
- ርግብ 18
- ኧረ ማን ነው? 19
- አንበሳው 19
- የጋራን በጋራ 20
- መደሻና ድንጋይ 22
- እግሩ እንደወሰደው 22
- የወዳጅ ምቀኛ 23
- መዝጊያ 24
- የሚያቃጥል ምግብ 24
- ማራቶን 25
- አይ ትምህርት! 26
- የድኩላ ዱለት 27
- ጊዜያዊ ፍቅር 28
- የምላስ ሃይል 28
- አቶ ደጉና ወ/ሮ ታመኑ 29
- የአሞሌው ጨው ታሪክ 32
- አገር ማለት ከብር 34
- የአበሻ ቀጠሮ 35
- በጊዜ ቤት ያልሰራ 36
- ሁሉን አውቃለሁ 37
- የውሸት እግሩ አጭር ነው 41
- ዕምነትና ክህደት 44
- የአበሻ ሥርግ 47
- የብልቂያጡዋ ታሪክ 49
- መተሳሰብ 50
- የአዳም ዘር በቀለም 51
- ትዝብት ነው ትርፉ 51
- ተንኮልና ይቅርታ 52
- ጉዟቸው ጎን ለጎን 54
- አይ ሥልጣኔ! 54

- አይጣልባችሁ 55
- ሰው የሚንቅ ሰው 59
- የአውሮፕላን ጉዞ 60
- ሰደት ያልሆነለት 61
- ድርሻህን ተወጣ 63
- የመማር ትርጉሙ 64
- ቀዩ ጥቁር ሲሆን 65
- የመሬት ለአራሹ ትዝታ 66
- ሃሳብ ከዘገየ! 69
- ኮዱ ጠፋ! 69
- የቁንጫና ትኋን ታሪክ 71
- የእናት ልጆች 73
- መተውን ወደድኩት 75
- ሰጡኝ ብቻ የሚያውቅ 76
- አባይ 78
- የውሸት ፈገግታ 78
- ከሽቶና ቀለም ውሃ ይቅደም 79
- ሥነ ምግባር 80
- የጋራ ምክር 81
- መጠጥ የማይፈታው 82
- እግዜብሔር ደስታ ነው 82
- ጉዟቸው ጎን ለጎን 83
- አገር የተሰፋ አገር 85
- በምላሱ ራቀ 86
- ሰው በሰፈረበት ጽዋ-- 87
- ሰው መድኃኒቱ 87
- ታላቅ ሃብት ጤንነት 89
- ዛሬም አልተማረ! 89
- የወሬ መቀስ 90
- በቀና መራመድ 90
- ምግብ ብቻ አይበቃም 91
- የይሉኝታ ታሪክ 91
- የዘመኑ ቅኔ 92
- በኢትዮጵያ የሐይማኖት በዓላት 93
- የሃሜታ ቤተሰብ 94
- ድንግል ማርያም 97







- ከምልክት በላይ 99
- ቅንዓትና ምቀኝነት 101
- ደስታና ምስጋና 102
- የድሮ ሃብታም መለኪያ 104
- አሜሪካን ድሪም 106
- የታርካብ ምስጢር 109

# መግቢያ

"Welt je nadhernα Kniha, aber nema Cenu pre toho nevie citat" ዓለም ድንቅ መጽሐፍ ነች፣ ነገር ግን ሊያነባት ለማይችል ዋጋ የላትም" የስሎቫክ ጥቅስ። ይህ ጥቅስ ሰዎች በሕይወት በመኖራቸው ብቻ ከሌሎች ሰዎች እና ከተፈጥሮ አያሌ ቁም ነገሮች ሊማሩ የሚያስችሉዋቸው ሁኔታዎች መኖራቸውን ያመለክታል። ዓለም አእምሮው ብሩህ የሆነ (open mind) ሰው ሁሉ ተምሮ ሊጨርሰው የማይችል ዕውቀት ይዛለች። የምታስተምረውም በነፃ ሲሆን በከፍያው ምትክ የምትጠይቀው ፈቅደኝነትን ብቻ ነው። አንዳንድ ሰዎች እከሌ ብልህና አዋቂ ነው፤ ሲባል ኮሌጅና ዩኒቨርስቲ ገብቶ የተመረቀ ብቻ አድረገው ይገምታሉ።

ሰዎች በምንም ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ይኑሩ ነገር ግን፤ አእምሯቸውን ክፍት አድርገው ከተነሱ ያለፈውን አስበው ፣ አሁን የሚገኙበትን አገናዝበው ለመጭው ለመዘጋጀት ኃይል ያገኛሉ። መኖር በራሱ አስተማሪም ት/ቤትም እንደመሆኑ የትምህርት ዕውቀትና በመኖር የተካበትውን ወርቃማ ልምድ ወደሚቀጥለው ትውልድ ለማስተላለፍ ሁሉም የቻለውን እንዲያበረከት የትውልድ ግዴታና አደራም ይሆናል። ለአገር ለወገን መቆርቆርን፣ መተባበርንና ቢጋራ ለማደግ ተስማምቶ መስራትን ተምሮ ማስተማር ያስፈልጋል። ዛሬ ዓለም የምታሳየን አንዱ ዕውነታ ልዩነትን አቻችሎ ሊጋራ ዕድገት የማይነሳ ሕዝብ ይሁን ድርጅት ተያይዞ እንደሚወድቅ ነው። በተለይም ዛሬ በከፍተኛ ፍጥነት እየጨመረ የሄደው የዓለም ሕዝብ ቁጥር እና እያቆለቆለ ያለው የምጣኔ ሀብት ሚዛን ሰዎች ከመቸውም የበለጠ ህብረት በመፍጠርና በመደጋገፍ መኖር እንደሚገባቸው ያሳሳበናል። እንዲሁም አስረካቢው ትውልድ በትምህርትና በኑሮ ያገኘውን ዕውቀት በፅሁፍ ዘክሮ ለተተኪው ትውልድ ማስተላለፉ አዲሱ ትውልድ ባለፈው ትውልድ ላይ ማህይም እንዳይሆን ይረዳል። ለአገር ለወገን ብዙ ታሪካዊ ሥራ የሰሩ ባለውሊታና የከፉ ቀን ልጆቿ ያደረጉትን መልካም ሥራ በቃል ከልጅ ወደ ልጅ ብቻ ሳይሆን በጽሁፍ ቢዘከር ለአገር ሁሉ ይዳረሳል። በዓለም ላይ ስትኖር ዘላቂነት ያለው መልካም ሥራ ለመሥራት ጥረት አድርግ፤ ታታሪ እና እንደ ርግብ ታማኝ ሁን፤ የቁም ነገር መካን አትሁን፣ ደካማና ተሰፋ የቆረጠ ሰው ዕድሜው አጭር ስለሚሆን ማምለጫህ ብርቱ መሆን ነው።

**ብዙአየሁ አበጀ**





## ◆ ጉንጭ አልፋው

ያልሆኑትን እንደሆኑ ያላደረጉትን እንዳደረጉ በማስመሰል ለማያውቋቸው ሰዎች በማውራት ራሳቸውን ከፍ አድርገው ለማቅረብ የሚሞክሩ ብዙዎች ናቸው።

እነዚህ ሰዎች ንግግራቸውም ጣዕም የሌለውና ጆሮ የሚያደነቁር፣ ጉንጭ የሚያለፉ ከመሆኑ ሌላ ርባና የለውም።

አንዳንዱ ቁም ነገር ሊያጫውተኝ ነው ብለህ ስትጓጓ ባዶ የሆነ ብሎም ያልነበረ የጉራ እና ራስን የሚክብ ጨዋታያቀርብልሃል።

አብዛኛው ሰው „ የምታወራው ምንም ስሜት አይሰጥም ወይም ራስህን ትክባለ በማለት ይቀርጣሉ፡፡

ትዕግስት ያለው ግን እንዲህ ዕይነቱን ሰው በመጣበት ዘይቤ መግቦ መመልሰ ራሱን የቻለ ጥበብ ነው። ይህን በሚመለከት በአንድ ጉዞ ላይ ሁለት ሰዎች ሲጫዋወቱ የነበረውን እናነባለን።

አንድ አውሮጳዊና አንድ ኢትዮጵያዊ ናቸው

አውሮጳዊው ፣ ሰላም እኔ ሳርኮቪች እባላለሁ!

አባሻው፣ የእኔ ደግሞ ማርቀስ ነው።

ብሎ ስሙን እንዳስተዋወቀ ፈረንጁ ቀጠልና በርካታ መንፈስ ጫንሙሉ ከተነፈሰ በሁዋላ ወደ አበሻው ፊቱን አዙሮ፤ አንተ በጣም ወጣትነህ ብዙ እድል አለህ ሲል፤ አበሻው ሰውየን ምን ነካው፤ ምንድን ነው የሚያወራው ብሎ ራሱን በራሱ ከጠየቀ በሁዋላ ሁለት እጁን እያመሳቀለ የምትለው አልገባኝም አለ።

ፈረንጅ የአገራችን ቋንቋ አትናገርም ማለት ነውን? ሲለው

አበሻውም በልቡ ኧረ ይህችን ይወዳል ! አለና ጥሩ አድርጌ ነዋ የምናገረው! አልገባንም ያልሁት የንግግርህን ይዘት እንጂ ቃላቱን አይደለም!

ታዲያ ምኑን አችላለሁ ትላለህ ቃላትን ገጣጥመህ አረፍተነገር ካልሰራህ ወይም የምናገረው ካልገባህ አለና ለማንኛውም እኔ ያሳለፍሁት ቆንጆ ህይወት እንዲገጥምህ እመኝልሃለሁ አለ።

አበሻው እስቲ ካሳለፍሃቸው ቆንጆ ነገሮች የተወሰኑትን ጥቀስልኝ።

ነጩ አለምን ተዘዋውሬ ለማየት ራሱን የቻለ ታላቅ ደስታ የሰጠኝ ስለሆነ ሌላ ተጨማሪ ማስረጃ የሚያስፈልግ አይመስለኝም። አህጉራት ተዛውሬ አገሮችን ጎብኛቸዋለሁ። አለምን ለመዞር አቅድ ሳወጣ ከተዘጋጀሁባቸው ነገሮች አንዱ በየአህጉሩ አስር አስር ቋንቋንዎችን ቀድሜ ማጥናት ስለነበር በአሁኑ ሰዓት ከሰባ ያላነሱ ቋንቋዎች እናገራለሁ" ።

ቀልዱን እንዳልሆነ መውሰዱም ጋብቻው፡፡
ተጋብተን ለመኖር ቃልሽን ያፈረሰሽው
ትምህርት ስንጨርስ ጥለሽ የጠፋሽው
ብዙ ዓመታት አልፈው ዛሬ ብቅ ያልሽው
ጥፋቱ ያንች ነው አንችው ያመጣሽው!
ከሚስትና ልጆቼ ጋር ደስ ብሎኝ እንድኖር
ሁሉን ባርኮልኛል ፈጣሪ እግዚአብሔር፣
በማለት አወራት በረከቱን ጨምሮ።
ውስጡዋ እያዘነ አፉዋን በእጁዋ አፍና
ታዳምጠው ነበር አልጨረሰን ገና።
ያለፈውም የአሁኑ እንደ ሕልም ሆነባት
አይን እንደፈጠጠ ሳይተኙ መቃዠት!
ባለፈው የሰራችውን ዞሮ እያስታወሰ
በቁጭት ንግግር ጋፋ ገሰገሰ፤
ኧረ ለመሆኑ እስቲ ልጠይቅሽ
ብዙ ዓመታት አልፈው እኔን ማስታወስሽ
ምን ሥሠራ ልቆይ እንዴት አድርገሽ ገመትሽ
እኔስ አልገባኝም የአሁኑ ሁኔታሽ!
ስለዚህ አድምጭኝ እኔም ሕይወት አለኝ
በኑሮየ የሚመጥ ትዳሬን የሚሰብር
እንኳን አሜሪካ የፈለገው ይቅር።
እያለ ሲናገር አሁን ተናደደች፣
እንደነበረ አልቆያትም ጥላው እንደሄደች!
ወይን የማትጠጣው ጠርሙስ ውስኪ አዘዘች።
ቁጣዋ ጨመረ ተራራ አከለች
ሂድልኝ ከአጠገቤ ብላ ገላመጠች
ትዕግስቱን ጨረሰ የእርሱም ቁጣ ወጣ
ጥፋቱዋን በመቁጠር ነጥቦችን አመጣ።
የተሻለ አግኝተሽ ጥለሽኝ ተሰወርሽ
ከዚያም ተመችቶሽ ኑሮሽን እየኖርሽ
ከስንት ዓመታት በኋላ ድንገት ከተፍ ብለሽ
ልክ ጥሬ ገንዘብ በባንክ እንዳስቀመጥሽ
በፈለግሽው ጊዜ የምትወስጅው አንስተሽ
እንደዚያ አይደለሁም እንደ አንች እኔም ሰው
መልካም ኑሮ ትዳር የሚርብ የሚጠማው፣
ስለዚህ አህቴ እኔ አላጠፋሁም
ትዳሬ ያልሽውንም እኔ አልበተንሁንም፣





ጊዜው ቢዘገይም እኔን በማሰብሽ
አመሰግናለሁ በይ ቸሩን ይግጠምሽ።
ብሎ ተሰናብቶ በዚያው ትቱዋት ወጣ
መቆየቱን ፈርቶ ጣጣ እንዳታመጣ።
አሁንም ስትባንን ቀርጠ ጥሉዋት ሲሄድ
ስህተቱዋን አስባ በጣም በመናደድ
እግሬን በሰበረው ምነው ከዚያ መንገድ
እኔው ስቅለበለብ ሲያቀብጠኝ መጥቸ
ይህው ጥሎኝ ሲሄድ ቀረሁ ተጎልቸ፡፡
በማለት ደጋግማ ራሱዋን ረገመች
እርሱን የሚተካ ሰው ማግኘት ወሰነች።
ትንሽ ስንባብታ ከተማ ስትዞር
አንድ ጎረምሳ አወቀች የሚዘል በአጥር
በተደጋጋሚ አብረው እንደወጡ
ቤርጎ እየቀየሩ ብዙ ተቀመጡ።
በጣሙን አፍቅራው ሁሉንም ረስታ
ወራት ተቀመጠች በሃሴት በደስታ።
አንድ ቀን እንዲሁ ከጠገቡዋ እንዳለ
ደከመኝ ብሎ ከዚያው ዘንበል አለ፣
አንተ አለኸኝ እያልሁ እኔንም አይዞሽ በል
እንውጣ እጅ ተነስ ደከመኝ አትበል።
አግብቸ ልወስድህ ሁሉን ተነጋግረን
የፈራህ መሰለኝ አበዛህ መድከምን።
ብላ ስታዋራው ምንም መልስ አልሰጣት
አቅም አጥቶ ነበር እሱስ በጣም አሞት።
ምንም ብታባብል ፍቅርዬ ብትለው
እንደምን ይመልስ ኃልም አልነበረው።
ትንፋሹ እያጠረ ድምጹ ስለራቀ
ዝም ያላት መሰላት ሆን ብሎ አያወቀ፣
አጥብቆ ዝምታው በጣም ሲደብራት
አብረን አንሄድም ወይ ወደ መጣሁበት?
ብላ ስትጠይቀው አሁንም ዝም አላት
ወደ እርሱ ተጠግታ በንዴት በቁጣ
አድርግልኝ አላልሁ ገንዘብ ከፈል አምጣ
መዝጋትህ ምንድን ነው ይህ ሁሉ ጣጣ!
እያለች ጉንጮቹን ስደባብሰው
ቀዝቅዘው ነበረ ወርዶ ሙቀታቸው

የአንባሳ ጠብ አይጣል ይመልሳል ጉድጉዋድ
ኢምንት የምታክል የአንበሳ ግልገል
ትልቅ ነው ብርታቱዋ ከአካሉዋ ያልፋል
ያን ፍርሃት አዝሉ ይኖር የነበረ
ንገሩት ያንን ሰው ለምንስ ደፈረ!
ሕግም ያሳገደው ድንበር ያልመሰሰው
ዝም ሲሉት የማይወድ መታረም የጠማው
በምላሱ አይሎ እውነት የመሰለው
አንተን አንቺ ብሎ ማናናቅ የሚወድ
ትናንትን ያልረሳ.የሚከዳ ዘመድ
ንብረቱ ሕይወቱ ሆዱ የሆነበት
ክብር እልባ ሆኖ የሚያሳጣ ክብረት
ከማስተማር ሌላ ምን አለው መድኃኒት?
ራሱን ጠብቆ ክልል አስከብሮ
እንዲሁ የማይተኛ ወሰኑ ተደውፍሮ
እንዲሁ የማይተኛ ወሰኑ ተደፍሮ
በአራዊቶች ሁሉ ስሙ የተፈራ
ዛሬም ያልታከተ ለክብሩ እየሰራ
ጉልበት አለኝ ብሎ በኃይል ሳይመካ
አንበሳው ይኖራል ማንንም ሳይነካ።
❖ ❖ ❖

## ♦ የጋራን በጋራ

ማን ነው ....ጠያቂ
ማን ነው ....ተጠያቂ?
አገር ....የጋራ
ሁሉም .... የሁሉ አደራ
በእድሜ ....ሳይለይ ጾታ
ሁሉም ....ዜጋ በተርታ
በማስተዋል ....በዝግታ
ለጋራ ....ችግርና ደስታ
ሁሉም ....ለሁሉ ካልተዘጋጀ
ልጅነት ....ምኑ በጀ?
እኔን ....ካልጎደለብኝ
አያገባኝም ....ምን ቸገረኝ





በዚህ ....አስተሳሰብ
ሞራል ....በማይስብ
አእምሮ ....ከዳሸቀ
የሚነሳው ....ከወደቀ
ተስፋ ....ቢስ ከተሆነ
አንድነት ....ከመነመነ
ሰው ....ለብቸኝነት ከተጠማ
አንድ ....ለመሆን ካልተስማማ
ብርሃን ....ሲተካ በጨለማ
ቁልቁል ....ሲሆን እድገት
ሲጋፉ ....ሞት ለሞት
ግለሰብ ....ሲያመካኝ በድርጅት
ድርጅት ....ደግሞ በመንግስት
መሊያችን ከሆነ . . . ድህነት
መሳለቂያ . . . ከሆንን በየሄድንበት
ማን ....ነው ተጠያቂ
ማን ....ነው ጠያቂ?
ሰው ....ሲነግሩት ካልሰማ
ለጋዜጣ ....ብቻ ከተጠማ
ሁሉን ....ሲወክል
ሁሉን ....ሲበክል
ሁሉን ....ሲያውቅ
ሁሉን ....ሲንቅ
እድሜውን ....የሚገፋ
የነቃ ሲመስለው. . .የሚያንቀላፋ
በየቦታው ....ሞልቷል
ምን ....ይሆናል?
ከራሱ ወደ ....ቀሪ አካላቱ
ሲዛመት ....ብክለቱ
ሰው ....ሲጣደፍ ለሞቱ
በምን ግዴ ....ዝም ማለቱ
የማን ....ነው ጉዳቱ?
የማን ....ነው ድክመቱ?
ሁሉም ....ከሆነ አዋቂ
አጥፊ ማን ....ነው ተጠያቂ?
ሰው ....ለራሱ እያደላ
ድክመቱን ....ሲፈልግ ከሌላ
ሆድ ....በሆድ ከሰፋ
ነገ ....በዛሬ ከጠፋ

በልቻ ሳልጠግብ ምራቄን ስውጥ
ለሳሳለት ሆዴ እድል የማይሰጥ
ይህስ ምን አይነት ነው የወዳጅ ምቀኛ
ሰላም ሳያሳጣ ሰላም የማይተኛ?
የደገፉ መስለው የተቆረቆሩ
ትዳሬን አፍርሰው እንደወጡ ቀሩ።
የእኔን ሳይኖሩልኝ እነሱን ሳልሆን
ወሬ ሲያቀብሉኝ ይሁንም አይሁን
አሁን ያሙኝ ጀመር ብቻየን ስሆን።
ተንኮል ከማዳመጥ ትዳርን በድሉ
ፍቅርን እያደሱ ወሬኛን አግልሉ
መኖር የመረጣል እድሜም ሳያረጅ
የወሬ መሰላል ለኑሮም አይበጅ።

## ◆ መዝጊያ



ከዋለበት ሲመለስ ቤቱ ለመግባት
ቀድማ የምትጠብቀው መዝጊያ የሚሉዋት
ውለታዋ በዛ ምን ባደረጋት?
ደከመኝ ሰለቸኝ ልተኛ የማትል
የጌታዋን ርግጫ ጡጫውን በመቻል
ሁሉን አሳልፋ ከዚያው ቅስቅስ አትል።
ቀንም ይሁን ሌሊት ክረምትና በጋ
ደረቱዋን አጋልጣ ስትጠብቅ ከአደጋ
ምንም አቻ የላት ቢዞሩ ፍለጋ።
መዝጊያ የሌለው ቤት፤ ካስገባ ሁሉንም
ከሆነ የአገሩ ቤት ተብሎ አይጠራም
ገበያ ነው እንጅ ወይም ስታዲየም።
ብረት ይሁን እንጨት ወይም የቆርቆሮ
ባለኤሌክትሪክ ይሁን ወይም የጭራሮ
መዝጊያ ነው ጠባቂው ቤትን ዞሮ ዞሮ።

## ◆ የሚያቃጥል ምግብ

ለምግብ ሲመኙዋት የምትከነክን
አጣፈጠው ቢያቀርቡዋት የማትተው ጸባዩዋን





ይህች ምን አይነት ነች ቃሪያ የሚሉዋት
መፋጀት የማትተው ከአመት እስከ አመት።
መልኩዋን አሳምራ ቀይ ቀለሙዋን ለብሳ
በርቀት ለሚያያት ታጉዋጉዋለች ደርሳ
ቀርበው ሲነካኩዋት አቃጣይ ነች ጭሳ።
እንደው ማሳሳቱዋ መልኩዋን አሳምራ
ውሃ ታሰኛለች ልክ እንደዋለ ሰው በጸሃይ ጠራራ።
አይ ቀዩዋ ቃሪያ ይህች ምን አይነት ነች
ውበቱዋን እያየች ብቻዋን የቀረች።
ፈትገውም ቢያጥቡዋት ለውጥ የማታመጣ
ሰው የማታስቀርብ ፍሬዋ ሲወጣ፤
በእውነትም ቃሪያ ነች ለሆድ የማትበጅ
ከቤት አትቻልም ትውጣ ወደ ከደጅ።
በየግሮሰሪው ብትውል ተሰጥታ
ሁሉ እያያት ቢሄድ ከጠዋት እስከ ማታ
ይሀን ትወዳለች ቢያደንቃት ሰው አይቶ
የሚላትን አታውቅ ወደ ቤቱ ገብቶ።
ቁም ነገር ካልሰራች ደስታን ካልፈጠረች
ቃሪያ እንዲያው ጌጥ አትሆን ለምግብ ካልዋለች
ራሱዋን ከፍ ብታደርግ ብትቀላ ብትደምቅ
ግን ተፈጥሮዋ ከሆነ አቃጥሎ ማስጨነቅ
ሁሉም ዋጋ ቢስ ነው ቀለም አይጠጣ
ከራስ ጋር ይኖራል ከራስም አይውጣ።
ለመንካት ሲፈራ ሁሉም አይቱዋት ያልፋል
ከቤቱ ቁጭ አድርጎ እሱዋን ሰው ማን ያያል።

## ◆ ማራቶን

ማራቶንሯጮች ውጭ አገር መጡና
እንሱን ለማየት እኔም ገባሁና
በሃሳቤ ስርጥ ከመሃል ገብቼ
በእጀ ስደበድብ ስመታ በእግሮቼ
እኔን እያላበኝ እነርሱ ሲሮጡ
በጣሙን ሲጨምር የልቤም ምታቱ



ጨኸቴን ለቀቅሁት በዝቶ መደሰቴ::
በሃሳብ ደክሜ ባለሁበት ስሮጥ
ጫን እየተነፈስሁ ደረቅ አየር ስውጥ
አንድ ነጭ ከአጠገቤ ተነስቶ በድንገት
አትጨኽብኝ አለ ዶንት ዱኢት ዶን ዱኢት
ተቆጣጠር ብየ ለራሴም ነግሬው
የሃገር ፍቅር ሲቃ ልቤ እንደት ይቻለው?
ገላምጨ እያየሁ እኔም የእነሱ ነኝ
ሁሉም ለየራሱ ከእቃም አልቆጠሩኝ::
በዞርሁበት አገር በተሰደድሁበት
በመልካም አንስተው ኢትዮጵያን ሲጠሯት
አይኔ እንባ እየሞላ በደስታ ስሜት
ይህችን አገሬን ከቶ ምን ሳድርጋት?
ያግሬን ባንዴራ በአንገቴ ጠምጥሜ
በአገሬ ስኮራ ስሟ ሆኖ ስሜ
በቁሜ እያለምሁ በአዕምሮየ ሳሰባት
የትም አገር ቢሄድ ምን ጊዜም አንድ እናት
በአገራችን ጉዳይ እንሁን ጠንካራ
የሚያስጠራ ሲኖር ሞልቷል የሚጠራ።
በርታ ተነስ ሩጥ ማን ነህ ባለ ተራ
አንተም ደስ ይበልህ በአንተ ስትጠራ::

## ◆ አይ ትምህርት!

ዓመታት ስቆጥር የችግር ጉዞየን
መቶ ሞላኝ መስል ሳስበው ድካሜን
አምላክ ካልፈቀደ ሰው ምንም ቢያደርግ
ጥረቱ አያሳካም አይችልም ለማደግ
በጣም ይገርመኛል አንዳንዴ ሳስበው
ሰው ካሰበው ቀርቶ ሲውል ካላሰበው
ብዙ ጥሬ ግሬ ሳልቆጥብ ጉልበቴን
ብዙ ዓመታት አልፈው ሳስበው እድገቴን
አዝናለሁ አንዳንዴ ካሰብሁት መቅረቴን
አምላክ ሆይ ባርክልኝ ቀሪውን ህይወቴን።
አንገቴን ደፍቶ እንዲያ እያጠነሁ
ሃምሳ ስድሳ ሳይሆን መቶ እየደፈንሁ
ከሁለት እንደኛ ልቆ ደረጃየ
ስሜ ተቀይሮ ቀለሙ ትብየ
አስራ ስምንት ሳይሞላኝ ያለአቅሜ ገስግሸ
በሚያስደስት ውጤት ሃይስኩል ጨረሽ
ዩኒቨርቲ ገባሁ ውጭ አገር ደርሽ።
ሳስበው የገርመኛል





አይ ድካም ያሰኛል
ከዲፕሎማ አልፌ ዲግሪ እንኳን ሳላገኝ
ፖለቲካ ገብቶ ለስደት ዳረገኝ።
በኖርሁበት አገር በተሰደድሁበት
መኖር መልካም ነገር ስንቱን አሳለፍሁት።
ኑሮየን ለመግፋት ስራ ተቀጥሬ
ሃሳቤን ሳልጨርስ ገና ተናግሬ
ከሚያጣጥሉ ጋር ሳልወደ ተጨምሬ
ስደቱ ሳይበቃኝ በዚህ መችገሬ።
ሳስበው ይገርመኛል
አይ አገር ያሰኛል
ስሜንና አገሬን ሙያየን ጠየቀው
መቸ ለምን መጠህ ሁሉንም አጣርተው
ፈገግታ ሲያሳዩኝ ያቀረቡ መሰለው
እንደራሴ መሰሎኝ
አሳቢ ባልሰጡኝ
የሆዴን አውጥቸ ሁሉን ነግሬያቸው
ይስቁብኝ ጀመር ከበር ወጣ ብለው።
ሲሉ ሰማሁዋቸው
ያንን ከተማረ ከዚህ ምን አመጣው
ሲካፈሉን ዝም አልሁ በጭቀው በጫጭቀው።
ሳስበው ይገርመኛል
በቅናት ጠፍር ወገቡን ጠንዞ
ስንቱ ይጨነቃል።
የሆነ ያልሆነ ከምሮ ከማምሮ
የተባለን ትቶ ያልታሰበን ፈጥሮ
ተንኮል ተከናንቦ ተንኮል እያፈላ
የእኔ ሆድ ጦም ቢያድር የእሱ ሆድ አይሞላ።
አንደኛ ብወጣ ብጎብዝ በትምህርት
በሙያየ አልሰራሁ በተማርሁበት
ምንድነው ቅናቱ እኔ ሳዘንሁት።
የልጅነት ዘመን የወጣትነቱን
ከዚህ እደርሳለሁ የሚለው ምኞቴን
ከፍላጎት አልፎ ያደርጉት ጥረቴን
ለድካሜ ሳልበቃ በህልም ለቀረሁኝ
የሰው ምቀኝነት ጭራሽ የማይገባኝ

## ◆ የድኩላ ዱለት

ሜዳውን የምትሄድ ጫካ የምትፈራ
ከቁጥቋ ጥ የምትርቅ ወይም ከታራራ
ከጅብና ነብር አምልጣ ከንበሳ
በስጋት የምትኖር ሳር ቅጠል በጥሳ
ወላጆቹዋ አልቀው በአንድ የጅብ መንጋ
በጣም የምትደክም እነሱን ፍለጋ
ድኩላ ነበረች ሌት ቀን የማትተኛ

ይወስድ ነበር ምኑንም ሳያስቀር
እንዳይሞቱ ያክል ከሚበሉት በቀር።
ባል አቶ ደጉና ሚስታቸው ታመኑ
ነጻ እንዲያወጣቸው እምላክን ለመኑ።
ከእለታት አንድ ቀን አቶ ደጉ ተነሱ
ስለ መብታቸው ጥያቄ አነሱ፤
የሚለበስ የለን ልጃችን አይማር
ለእርሱ እድል ይሰጠው እኛስ እንቸገር፤
ዘመኑ ከአፈራው እውቀት እንዲካፈል
እባክዎ ይስጡት የመማር እድል።
ይህን ቢጠይቁት ጭራሹን ተናዶ
ሁሉንም ሊያባርር ተዋቸው ተማልዶ።
ልጁም የተመኘው የትምህርት ህልሙ
ነፋስ ሆኖ ቀረ በነነ በቁሙ።
አመታት አለፉ አባትም ደከሙ
አልጋ መዋል ጀመር በጣሙን ታመሙ፤
ልጁ ተተክቶ በአባቱ እግር
የቤት ራስ ሆኖ ገብሮ ሊጦር
እጣው ይህው ሆኖ ማረስን ጀመር።
ታመኑ ነበሩ በጣሙን ጠንካራ
ጉልጓሎና ወፍጮ ሌላም ብዙ ስራ
ስለበዛባቸው አቅማቸው ደከመ
ቀኑ ሆነባቸው ሳይመሽ የጨለመ።
ሃይል ተሳናቸው ውሃ ለመቅዳት
የሚረዳ የለ ሴት የሚልኳት።
እንደዚህ ሲኖሩ በእድል እያዘኑ
ያች የአስገባሪ ሚስት አጉል የዘመኑ
መስራት ከአልቻሉ ቦታ ይለቀቁ አሉ።
ጌታውም ተስማሙ ይህ ሃሳብ ፀደቀ
ቦታውን እንዲለቁ ክረምቱ እንዳለቀ።
ጊዜ ተጣዳፊው ከአልነቁ የሚያመልጥ
ክረምቱ አለፈ አንድም ሳይጨበጥ።
ወጣቱ ጌታውን ሄደና ለመነ
ጊዜ ይስጡን ብሎ ወድቆ ተማፀነ።
ማረፊያ ፈልጎ ወላጆቹን ሊወስድ
እሽ ብሎ ሄደ ከቀየው ሊሰደድ።
በአካባቢ ከአለች አንዲት ከተማ
ዘበኝነት ገብቶ ድምጹን ሳያሰማ
ቀን ቀን ብቅ እያለ ወደ ወላጆቹ
ምስጋና አግኝቶ በቀጣሪዎቹ
መንፈቅ እንደሰራ የሌሊት ጥበቃ





ትልቅ ክፍል ሰጡት ለሶስት የሚበቃ።
ስለ ወላጆቹ ነግሯቸው ነበር
አሁን ፈቀዱለት አምጥቶ እንዲኖር፤
ወላጆቹ ገና በአምሳዎች ነበሩ
የወደቁ ያለ እድሜ ያለ እረፍት ሲሰሩ።
የተሻለ ምግብ እረፍት ትንሽ መድሃኒት
አግኝተው በረቱ ይህ ነበር ያጡት።
አመት እንደቆዩ ተከራይተው ወጡ
እጅግ አመስግነው ስላወጧቸው ከማጡ።
ልጃቸው ቀጠለ በዘበኝነቱ
እያመሰገነ ስለ እናት አባቱ።
ፊደል ያልቆጠሩ ተፈጥሮ ያስተማራቸው
ዘመናዊ ገበሬ አቶ ደጉ ናቸው።
አንድ ቀን ቁጭ ብለው ሶስቱም ጫወቱ
በጣሙን አመሹ ነጋጋ ሌሊቱ።
እንደነርሱ ያሉ በግፍ የተጣሉ
ሰምተው አውቀው ነበር ብዙዎች እንዳሉ
ለማግኘት ወሰኑ በጋራ ለመሥራት
ህብረት ምንም ቢሆን አለውና ውጤት።
በሰው በጎረቤት ለሁሉም አዋርተው
እንዲሰባሰቡ ክፊሉን አሳምነው
ቆዳ እያለፉ ለመሸጥ ተስማምተው
ሥራው ሳይጀመር ሁሉም ሸሹ ጠልተው።
ጠንካሬ አቶ ደጉ ህልም የነበራቸው
ተስፋ ባለመቁረጥ ሳይወድቅ ሞራላቸው
ትንሽ በያዙዋት ብር ቀጠሉ ለብቻቸው
አንድ ሁለት እያሉ ጀመሩ በትንሹ
ህብረቱ አልሰራም ሁሉም ስለሸሹ።
ጥረታቸውን ያየ አንድ የሰፈር ሐብታም
ፍንከች አይወጣውም የሚባል ስስታም
በባዶ እግራቸው ቆዳ ሲያለፉ አይቶ
ቆዳ ማለስለሻ በራሱ ወጭ ገዝቶ
ሰራተኛ ልኮ ከቤቱ አስጠራቸው
ሥራ ተገኘልኝ ብለው ደስ ብሏቸው
ምኞታቸውን ሊሰሙ ሄዱ ተከትለው።
ሐብታሙም በደስታ ተነስቶ ተቀበላቸው
የጥሪውን ምክንያት ዘርዝሮ አስረዳቸው።
ከልብ ደስ ብሏቸው ከጫማው ሲወድቁ

ሳንቲም እየተቀበልኩ ብዙ ጊዜ ረድቻታለሁ። እርሱዋ ግን ያን ጊዜም ገንዘብ ደልቷት እንደምትኖር ሆና ለመታየት ያን ጊዜም የማታደርገው ጥረት አልነበረም። ስትል እኔም፣ አሁን ስለ እርሷ ማውራት ለምን አስፈለገ ? ብየ ጠየቅኋት።

"ስለ እርሱዋ ማውራት የፈለግሁበትን ምክንያትማ ልነግርህ ነው፣ ምነው አንተ ደግሞ ተጣደፍህ ለወሬ ሞትኩ ሆንህብኝ፣ ኦከይ ዝም ብለሽ ጨዋታውን ቀትይልኝ አልኳት፣

"አንድ ቀን ከተማ ከታላቅ ወንድሜ ጋር አንድ ዕቃ እንድንገዛ ታዘን ስንሄድ በድንገት ሙሪትን መንገድ ላይ አገኘናትና ሰላምታ ተቀያየርን። እኔም ከተያየን ብዙ ጊዜ ሆነን ስላት አዎ አንችነሽን ላጠፋሺ ትንሽ ቀርቶኝ ነበር ስትል ተሳሳቅን። ከዚያም ወደ እኔ ጎን ጠጋ አለችና ወንድሜን በመሸከርመም እያየች "አንች ይህን ሎጋ ከየት ጠለፍሽ?" ስትል የልጠበቅኩት ንግግር ስለነበር ደነገጥኩ፣ እይ ይህማ ታላቅ ወንድሜ ነው አልኳትና፣ አንቺ አሁንም ያው አይን አውጣ ደፋር እንደሆንሽ ነሽ በማለት ድንጋጤየን በፈገግታ ለማጣጣት ሞከርኩ። ወንድሜ ግን ላለማሳፈር ሲል፣ ምነው ዕውነቷን ነው ምን ይወጣልኛል? ሲል የባሰ አሳፍሮኝ ቁጭ አለ።

ተሳሳቅንና እኔም በተራየ አንችስ በአገር አለሽን ብየ ስጠይቃት ፣ ወዲያው ቀጥላ አንገቷን ወዲህና ወዲያ እያወዛወዘች " ከቤቴ ወጥቼ የምዝናናበት ብዙ ጊዜ የለኝም" አለች።

ቀጥላ ለንግድ ሥራ ማካሄጃ ጭምር ይሆናል ብየ ትልቅ ቤት ስለተከራየሁና ንግዱን ከፍቶ በዚያ ቤት ስለማካሂድና እንግዳም ስለሚበዛ የጊዜ እጥረት አለብኝ" አለች። ጨዋታን ጨዋታ ያመጣዋልና እኔም ቀጥየ ፣ ለመሆኑ ምን ዓይነት ንግድ ጀመርሽ ብየ ጠየቅኋት። የምሠራው ምግብ እያዘጋጀሁ ለሚሸጥ አንድ ድርጅት ማቅረብ ነው።

ለየትኛው የንግድ ድርጅት እንደማቀርብ ግን አትጠይቂኝ። ኮንትራቱን ከሰጠኝ ድርጅት ጋር ምስጢሩን ለመጠበቅ ውል ፈርሜያለሁ። ስትል ወንድሜ ቶሎ ብሎ ተያት በቃሽ አትጠይቂያት እያለ በዕይኑ ምልክት ቢሰጠኝም ሁኔታዋ ዝም የሚያሰኝ ስላልነበረ በጥያቄ አጣድፍኋት። በዚህ ምክንያት " ጎበዝ ነሽ, ለመሆኑ ምን ዓይነት ንግድ ጀምረሽ ነው ብዬ ጠየቅሁኋት፤ የምግብ ንግድ ነው " ምግብ እየሰራሁ ለሚሸጡ ማቅረብ ነው" ይህንንም የማዘጋጀው ከቤቴ ስለሆነ ይህንን እንዳደርግ ማዘጋጃቤቱ ስለማይፈቅድልኝ ኮንትራት የሰጠኝን ድርጅት ስም እንዳትጠይቂኝ" አለች። ከዚህ በተጨማሪ ከድርጅቱ ጋር ኮንትራት ውል ስፈራረም፣ ይህንን በሚመለከት የፈረምኩ በመሆኔ ነው።

እኔም ይቅርታ እንደዚህ ሆነስ ልክ ነሽ አትንገሪን ይቅርብን በማለት ከምትለው ነገር ለመሸሽና ለመስማትም እንደማንፈልግ አረጋገጥኩላት።

በዚህ መካከል አንድ ሴትዮ የሙሪትን ስም በርቀት እየጠሩ በቁጣ ወደ እኛ ሲመጡ አየናቸው።





ሙሪትም የሴትዮዋን ጩኸት ስትሰማና ስታያቸው ደነገጠች። ቀጥላም "አሁን ደግሞ ምን ልትለኝ ነው" ብላ ንግግሯን ሳትጨርስ ሴትዮዋ ደረሱና " አንቺ ክብር ሲሰጠሽ ክብር የማይወድልሽ ምን ዓይነት ሰው ነሺ? በጠዋት ወጥተሽ በዚያው ትቀሪያለሺ እንዴ? ሽንክርትና ዘይት ገዝተሽ እንድትመጭ ብር ሰጥቸሽ ቀኑን ሙሉ የጠፋሽበት ምክንያት ምንድን ነው? ብለው ሲያፈጡባት እንደ ዕቃ የሚጫወቱበት ሌላ ሰው ይፈልጉ አለችና ቻውም ሳትለን ሄደች።

ሴትዮ ወደ ሄደችበት ትክትለው፣ ስሚ እኔ እኮ አልችልም ብትይኝ ጥሩ ነበር፤ ገንዘብ ተከፍሎ የሚሰራና ሥራም የሚፈልግ ብዙ ሰው አለ። አሁን መጣሁ እያልሽ በየቀኑ ግማሽ ግማሽ ቀን ጠፍተሽ ትውያለሽ። እኔም ግን በአንች ምክንያት በየቀኑ ደንበኞችን እያጣሁ ነው።" ልብስሽንና ጫማሽን መጥተሽ እንድትወስጅና ቤቴን እንድትለቂ እያሉ ይናገራሉ እርሷ ግን ርቃ ሄዳለች።

እኛም ከመጀመሪያው የባሰ ተገርመን። ሙሪት ከደቂቃዎች በፊት ስታወራን የነበረውና አሁን ደግሞ ሴትዮዋ የሚናገሩት ነገር ግራ አጋብቶን ነበር።

ወደ እኛ ዘወር አሉና፣ እናንተ ለመሆኑ ጓደኞቿ ናችሁን? ሲሉ ሳናስበው ጥያቄ አቀረቡ። እኔም አዎ የድሮ ጓደኛየ ነበረች፣ አሁን ግን ከዚህ በድንገት የተገናኘነው ከሁለት ዓመታት በኋላ ነው። አልኋቸው። አስተያየታቸውና አነጋገራቸው የሚሰፈራ ነበር።

ወንጀል ያለው ነገር ሰርታባቸው እንደሆን በልቤ እየሰጋሁ።

ቀጠሉና" በቃ ይኸው ነው! ለሰው መልካም ነገር ማድረግ ውጤቱ እንደዚህ ከሆነ እንዴት ተደርጎ ሰው ማመን ይቻላል። ይህች ልጅ ሳገኛት "ወላጆቼ በልጅነቴ ስለሞቱ የደም ዝምድና የሌላቸው ሴትዮ አሳደጉኝ። እርሳቸውም በዕድሜ ምክንያት ሲሞቱ በየሰው ቤት እየተጠጋኩ በሠራተኛነትም እያገለገልሁ መኖር ተገደድኩ። ትምህርቴንም ተከታትዬ ለመጨረስ አልቻልሁም። ስትል አንጀቴን በላችኝ። በጣም አሳዘነችኝና በይ በስራም ታግዥኛለሽ ቦታ አግኝተሽ እስከ ምትሄጂ ለጊዜው እረዳሻለሁ" ብየ ቃል በገባሁላት መሰረት እንደ ልጄ አድርጌ ስንከባከባት ነበር" አሉ።

ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ ብር እና ዕቃ እየጠፋብኝ ተቸግሬ እንዳለሁ አንድ ቀን ስከታተል ገንዘብም የምትወስደውና ዕቃም እያወጣች የምትሸጠው እርሷ እንደሆነች ደረስኩበት። ለፖሊስም ላስይዛት ስነሳ ይማሩኝ ይቅር ይበሉኝ በማለት ከእግሬ ሥር በመውደቅ ፖሊስ እንዳልጠራ ለመነችኝ።" እኔም አልፍሁዋት። እርሷ ግን መሰረቷን አልተወችም። ይባስ ብላ በየወሩ እየከፈሉ የምቀልባቸውን ደንበኞቼን በብዙ መንገድ አራቀችብኝ። በቅርቡ ደግሞ የያዘችው ፋሽን የተላከችበትን ዕቃ ገዝታ መመለሷን ቀርቶ ውላ ትመጣና የምትሰጠው ምክንያት ገንዘቡ ጠፋብኝ ነው። አሉና፤

ለመሆኑ እናንተ የማን ልጆች ናችሁ ? ቤታችሁስ የት ነው ? በማለት ጥያቂያቸውን ሲደረድሩብን „ እኒህ ሴትዮ የሌባ ተቀባይ ናችሁ እንዳይሉን ፈርተን፣ በሉ ማዝር ደህና ይዋሉ ብለን ትተናቸው ተፈተለክን። እኛ ወንጀል

የፊፀምን ይመስል እየዞርን እያየን ተጣድፈን ሸሸን። ወይ ሙሪት! „የውሸት እግሩ አጭር ነው ።" የሚባለውን ዛሬ አየነው ብለን ተሳሳቅን።

## ◆ ዕምነትና ክህደት

ክህደት አንድ ቀን ሲሄድ ብቻውን
ጮክ ብሎ ተጣራ እየና ዕምነትን።
ስፈልግህ ነበር ሰሞኑን ያለ ዕረፍት
እስቲ ቁጭ ብለን ትንሽ እንጫዎት!
ዕምነቱ ተሰማማ ትክሻውን ሰብቆ
ምክንያቱን ሳያውቅ ክህደትን ጠይቆ።
የዕምነይም ቤቱ ቅርብ ስለነበር
ተያይዘው ሄዱ ሌላ ቀን ሳይቀጥር።
እንደምታውቀው ጊዜው በጣም ከብዱዋል
ለብቻ ለማደግ በጣም ያስቸግራል።
ስለዚህ ዕምነቱ ከተስማማህበት
አብረን ብንሰራ ሆነን አንድ ጉልበት
በማለት ሃሳቡን አጣፍጦ አቀረበ
ዕቅዱን በውስጡ ልቡ እየሸረበ።
ዕምነቱም በደስታ እሺ ይሁን አለ
የወዳጁን ሃሳብ አምኖ ተቀበለ።
አብረውም ለማደግ በአቀዱት መሰረት
ያላቸውን ገንዘብ ሰብስበው በአንድነት
ዕምነት ሻጭ ሆኖ ገንዘብ ያዥ ክህደት
ትንሽ ኪዮስክ ከፍተው ተጀመረ መስራት።
በሶስት ቀን አንድ ጊዜ ሲታሰብ የተሸጠው
የሚያሳስብ ነበር በዛ የሚጎድለው።
ክህደት እያወቀ እየሳቀም ልቡ
ብሎ ይጠይቃል የት ገባ ገንዘቡ?
ከሱቅ የምንውለው ሆኖ ሁለታችን
እኔ ከአላነሳሁ ማን ያማዋል መነን?
በማለት ክህደት ሲናገር በድፍረት
ዕምነትም ዝም ይላል ጭቅጭቅ ሰልችቶት።





ይህ በዚህ ቀጥሎ ዓመት እንደሰሩ
ኪሳራው ቀጠለ በጠብ ተማረሩ
የበለጠችግር ክህደት ሳያመጣ
ዕመነት ከገባበት በቃኝ ብሎ ወጣ።
ክህደት ደስ አለው ሱቁን ጠቀለለ
እንደ እኔ ማን አለ በጣም የታደለ
እንድ ቂል አግኝቸ አክስሬው ወጣልኝ
ዓመት ጉድ ሰራሁት በነፃ ሰራልኝ።
እያለ ገንዘቡን ይቆጥር ነበረ
የዕመነት የዓመት ድካም ሁሉን ሳላስቀረ።
ከቤቱ ደብቆ ባንክም ሳያስገባው
ሰው አያምንምና ባንኩም ለእርሱ ያው ነው።
ትንሽ ሰነባብቶ አንድ ሴት አስገባ
ትረዳው ነበረ ምግብ ማዘጋጀት በልብሱም አጠባ።
አንድ ሳምንት ቆይታ ቤቱን ስታፀዳ
ፍራሹ ላይ አየች አያሌ ቀዳዳ
የማይጠቅሙ ዕቃዎች መጣያ ቀን ነበር
አሮጌውን ፍራሽ አወጣችው ከበር
ወደ ሱቅም ሄዳ አዲስ ፍራሽ ገዛች
እርሱን ለማስደሰት በልቡዋ እያሰበች።
ውስጡ እየቀፈፈው መንፈሱ እየባባ
ከስራ ሲመለስ መኝታ ቤት ገባ
ቅር ቅር ይለኛል ምን ምንድን ረሳሁኝ
ሰመጣ ጀምሮ ራሴን ከበደኝ
በማለት ሲያዋራት ሳሎን ተመልሶ
ተታልየ እንዳይሆን አለ ከእርሱም ብሶ!
ሶፋውን አዞርሽው አለ ቀጠለና
ቦታውን ቀይራ አጽድታው እየና።
ሶፋ አስተካክየ ፍራሽ ቀይሬያለሁ
ያን የተቀደደ አውጥቸ ጥያለሁ
ያን ጊዜ ደንግጦ መኝታ ቤት ገባ
እንሶላውን ሲገልጥ በጣም እየባባ
የፈራው አልቀረም ያኛው ፍራሽ የለም
ፍራሹ ውስጥ ነበር ገንዘብ ሲያጠራቅም፣

እግዜር ያውቃልና ደግሞ ለሚመጣው::
ለጠጅ ለጠላው ለምግብ ለአረቂው
እጅግ ብዙ ወጣ ለአስር መቶ ሰው::
ሰርጉ ተደረገ ሰባት ቀን ተበላ
በስምንተኛው ቀን አልቀረም አተላ::
ሰርጉ ተፈጥሞ ወራቶች አልፈዋል
ሜጉላው ድሮ ፈርሶ ወደ ቤት ገብተዋል::
ለሰርግ የታረደ ቆሞ አያርስ ነገ
የእርሻ ወቅተ ደረሰ ጉልበት አስፈለገ፤
እንደምን ይታረስ አጣማጅ ጎደለ::
ጊደር ብቻ ቀርቶ የወተት ላም የለ፤
ጥጆች ገና ለጋ አይችሉ ለማረስ
አሟጦ ወስዶታል የሰባት ቀን ድግስ::
የልመና በሬ እየተቀናጀ
መሬት ጦም አደረ ሳይታረስ ባጀ::
ጊዜውም ሮጠ ሆነ ሁለት አመት
በሬም አልተተካ ወይም እም ለወተት::
ቀጥሎ ያለው ልጅ አለ ካልተዳርኩ
ሆኘ እቆጠራለሁ ቆሜ የቀረኩ
ስለዚህ አባቴ ከምባል ቆሞ ቀር
ቶሎ ዳረኝና አንተም በእኔ አትፈር
ጥቂት ሰዎች ጥራ አስር መቶው ይቅር::
በማለት ልመና አቀረበ ደግሞ
የሚመጣውን እዳ አላየም ፈጽሞ::
ሚስትና አቶ እከሌ ብዙ ተማከሩ
መፍትሄ አላኘገም አያል ነው ችግሩ::
የት ሰው ተጠርቶ የትኛው ይቀራል
እነከሌን ብንተው አገርስ ምን ይላል፤
ለመጀመሪያው ሰርግ ብዙ ስለወጣ
የአንተ ሃሳብ ደግሞ ፈጥኖ ስለመጣ
በዚህ አጭር ጊዜ ከወዴት እናምጣ
ስለዚህ ልጃችን ቆይ ጥቂት አመት
እርሾ እንዳናጣ እንዳንሆን ባዶ ቤት::
በማለት ሊመክሩት ሞከሩ በጋራ
እርሱ ግን አዘነ ልቡ እንደ መከራ!
ከዛሬ ጀምሮ በቃኝ ከአንተ ጋራ
ብሎ ከቤት ወጣ ጋቢውን ጠቅልሎ
እንደገና ወደ ቤት ላይመለስ ምሎ::
እናት ብትለምነው እግሮቹ ስር ወድቃ
እምባ ብታነባ ለመጭው ተጨንቃ
እንደገና አለ አትድከሚ እናቴ





ተመልሼ እመጣለሁ ሲሟላ ምኞቴ:
በዚህ ንግግሩን ጨረሶ ተጓዘ
ተመልሶ አልመጣም መሽ ደበዘዘ::
አጠር መጠን ብሎ ሁሉም ቢዘጋጅ
ሃይል ገንዘብ ጊዜ ያለአግባብ አይፈጅ::
በአደጉት አገሮች ሃብት በሞላቸው
ገንዘብ ተትረፍርፎ ቢኖሩም ደልቷቸው
የሚታወቅ ሁሉ አይመጣም ሰርጋቸው::
ከሃብት የለንበት ነን ከችግረኛው
ከአቅም በላይ ሰርጉ ምን ይባላል የእኛው?
ባሕላችን እያልን ሁሉን ከነተትን
እንዴትስ ይጨምር እድገት ፍጥነቱን?

## ♦ የብልቂያጡዋ ታሪክ

ልምድ የለኝ የቆየ በአየር የመብረር
ለእኔ ብርቅ ነበር መኪናም በምድር::
ስለጠንኩ ስል ነበር ፊደል ስለቆጠርኩ
አውሮፕላኑ ውስጥ ለራሴ ሞኝ ሆንኩ::
የተሰራሁትን በአጭሩ ላውጋችሁ
እናንተም እንዲሁ ይሆናል ገጥሟችሁ!
በአንድ ሰሃን ነገር ምግብ እንደተሰጠኝ
ግማሽ ሰዓት ቆየሁ አበላል ጠፍቶብኝ::
እኔ የለመድኩት እንጀራ በወጥ
የመጣልኝ ደግሞ የሚቀባ ነገር ስጋና ብልቂያጥ::
ቢላዋ አልቀረም ሹካ ማንኪያ ጭምር
ደግሞም የታሸገ አንድ ትንሽ ነገር፤
ትንሽ ጠርሙስ ውሃ ያች ብልቂያጥ ጭምር
ደርድራ አመጣች ከየቱ ልጀምር?
እንዴው ፈራ ተባ እያለብኝ ሆዴ
ለብቻ ዳቦውን በላኩት በግዴ
ዳቦው ከጉሮሮ ቢለኝ አልወርድልህ
ጠርሙሱን ከፍቼ ጨለጥኩት በእልህ::
ያችን እሽግና ብልቂያጥ አስቀርቼ
ሌላውን በሙሉ ሰጠኋት መልሼ::
አምጣው እንደምትለኝ እፍጥጬ ሳያት
ዱ ዩ ዋንት ሰምሲንግ ስትል ደንግጬ ኖ አልኳት!
እርግጠኛ ሆኘ በብልቂያጧ ሽቶነት
እንዴያውም ወሰንኩኝ እዚያ ላለመክፈት::

ባልቤ እያሰብኩ አይ ሃብታምነት
ምን ቢደላቸው ነው ሽቶ ያደሉት
ምግብና መጠጥ በነጻ እዎደሉ
ለእያንዳንዱ ሽቶ ብልቂያጥ መታከሉ፤
እያልኩ ለብቻዬ ሁኔታውን አደነቅኩ
ከእጅ ቦርሳየ ውስጥ ብልቂያጧንም ጨመርኩ::
ጉዞ ተጠናቆ ደርሸ ከቤት
ቸኩየ ነበር ከቸቸ ላሸት::
ጠዋት ተነሳኩና መፈላሰፍ ጀመርኩ
ያች እሽግ ነገር ምንድን ትሆን እያልኩ፤
እንዳትበአሸብኝ ቀስ ብየ በሰልት
ያችን ባለምስጢር እስግ ከፈትኳት
የሎሚ ሽታ ያለው ርጥብ ወረቀት
በሙሉ ስከፍታት ተጣጥፎ አየሁት::
ለካስ ይህ እሽግ የአፍ መጥረጊያ ኖሯል
እነደ እኔ ያለውን ስንት ሰው አታሏል?
ተሎ ተነስቸ ብልቂያጧን አመጣኩ
የእርሷንም ሽቶነት ስለተጠራጠርኩ፤
እንዳትከፍት ተብየ እንደተነገረኩ
ጨብጫት ለመክፈት ፈራ ተባ እያልኩ
ከፍቸ እንድወረድ ለራሴው ነገርኩ፤
ቀስ አደረግኩና ከፍቸ ሳሸታት
ደግሞ የምን ሽቶ ብልቂያጧስ አልኮሆል ናት:

## ♦ መ ተ ሳ ሰ ብ

እሰቲ እንደጋገፍ አንዱ ለአንዱ ይስብ
ከመጎተት ይልቅ ወደታች ከመሳብ
ድክመትን ማካረር ይቅር ስም ማጥፋቱ
ስንት ጉድ ሽፍኖ ሁሉ በየቤቱ !
ጥሩውን እናስብ እሰቲ እንረዳዳ
መጠላለፍ ቀርቶ ትተነው ከጓዳ
አንዱ በጎ ሊያደርግ ከልቡ ሲነሳ
ማንኳሰሱ ይቅር ፈልጎ ጠባሳ::
እኔ አልቻልሁም ብሎ ሌላውን ማጣጣል
ሁሉ ቢደነቁር ለማንስ ይጠቅማል!
የሁሉስ ድህነት መፍትሄ ይሆናል?
አንዱ ያልቻለውን ሌላው ሲሳካለት
ምቀኝነት ይቅር ጠላት አድርጎ ማየት::





## • የአዳም ዘር በቀለም

እግዚአብሔር ፈጠረው ሰውን እንደ አምሳሉ
እርሱም አንድ ነበር ስናውቅ በከፊሉ
አዳም የተባለ የመጀመሪያው ሰው
ከእርሱ አጥንት ወስዶ ሄዋንንም ሰጠው::
በኋላም ቆይቶ ትውልድ ተባዛ
ሰውም ተበተነ ምድርንም ገዛ::
የአዳም ዘር በቁጥር እያየለ ሄዶ
ግድያ ጀመረ አንድ መሆኑን ክዶ
ይህም አልበቃ  አለው ተንኮሉ ጨመረ
በነገድ ደረጃ ዘር እየቆጠረ::
ከአንድ አስራሁለት ከዚያም አእላፍ
አደገ ችግሩ ተሰራ ጠረፍ
በዚህ አላቆመም የአዳም ልጆች ዘር ተባላ እንደገና
ነገድ ጠረፍም አልበቃው አለና::
ከጎሳም ከነገድ ከአገርም ዘሎ
መጠራት ጀመር በአህጉር ተጠልሎ::
ደግሞም ይባስ ብሎ ቀለምን አመጣ
ነጭ ቢጫ ቀይ ጥቁር የሚሉትን ጣጣ::
መድልዎም ጨመረ ቀለሚጠ ሲጎላ
ቀለም ለቀለሙ ሆነ የሚያደላ::
ይህም ችግር ደግሞ ቀለበትን ሰራ
ሰው ምንጩን ረስቶ ሆነ ባላንጋራ::
ሌላ ችግር መጣ በዚያው በአንድ ቀለም
እጅግ የሚያባላ ወንድምን ከወንድም
እርሱም ሃይማኖት ነው ብዛቱም እልቅ የለው
እግዚአብሔር አንድ ነው ሰው ግን አበዛው::
ማምለኪያንም ሰራ ሕዝብ በየእምነቱ
ጣኦትም ገነነ ሰው ሸሸ ከእውነቱ::
እውነት እግዚአብሔር ነው ሰውን የፈጠረ
ለሚያምነው የሚያድን አማኝ ያከበረ::

## ♦ ትዝብት ነው ትርፉ

ጆሮዬ ሲሰማ አልሁት ሆዴን ቻለው
አልፎ አልፎ ሲረክስ የመናገር ዋጋ
ትዝብት ነው ትረፉ ሰው ማንሳት መጣሉ

ነፍሱን ከነስጋው በሃሜት ማቃጠሉ።
አልብላው ይቅርብኝ ከወሬኞች ጋራ
ሆዴም አይቀበል የነገር ጨንራ።
ከአደንቋሪ ወሬ ትምህርት ከሌለበት
ይሻል ይመስለኛል የብቸኛ ሕይወት።
ውቅያኖስ ሆነ ሆዴ በጥልቀቱ
ሁሉን ችሎልኛል ቢበዛም ትዝብቱ
ምንም የማያውቁ በምላስ የላቁ
እኔስ ሰምቻለሁ በእግዜር ሲሳለቁ።
በትዝብት እንዳላልፍ መንፈሴ አስገድዶኝ
መሳለቁን ተው በአምአካችሁ አልኩኝ።
መቸም ኑሮ ካሉት መቃብርም ይሞቃል
ጊዜ የሰጠው ቅል ድንጋይን ይሰብራል።
እኔም ኑሮ ብዬ ያዝኩት በሰፊው
አንገቴን ደፍቸ ጊዜ ለሰጠው።
ከፉም ከምመልስ ይቅርብኝ ጨዋታ
ትዝብት ነው ትረፉ ኪሳራው ቅሬታ።
በጎ ላድርግ ብሎ ሰውን ሲረዱት
ይውል ያድርና ይሆናል ጠላት።
ስንቱን ሰው ታዘብኩት !
ሲለወጥ እንደ እስስት !
ብዙ ነገር ተማርሁ በአለፈው ዕድሜየ
እሰቲ ልመዝግበው ይውጣ ከዓዕምሮዬ።
ብዙ ሃብትም ሆነ የሰላ ምላስ
አያገለግልም ውሉ ቀን ሲደርስ።

## ♦ ተንኮልና ይቅርታ

ከዕለታት አንድ ወቅት በተንኮለኞች መንደር
ይቅርታ የሚባል አብሮ ይኖር ነበር፣
አንድ ቀን ተንኮለኞች ተንኮል ሲጫጭሩ
ይቅርታን ከቤቱ እንዲወጣ ጠሩ።
አልገባውምና ምክንያቱን ጠየቀ
ምንስ እንዳሰቡ ከቶ የት አወቀ!
ድግስ አለን አሉት እስክሲታ ጭፈራ
አልሄድም አላቸው መጨውን ስለፈራ።
እጅግ ወተወቱት እንዲሁ አልተውትም።
አባብለው ለመውሰድ ብለው እንደምንም
አልኮሆል እንደማትቀምስ እኛም እናውቃለን





ለሰላሳ ለብቻህ እናዝልሃለን
በማለት አዋክበው ወሰዱት ጎትተው
በሁዋላ ደረሰ መች ቀረ የፈራው!
ለሰላሳ ቀርቦለት ከአፉ ሳያደርሰው
የተንኮለኞች አለቃ ቀማና ወሰደው።
ይህስ ለምን ሆነ ይቅርታን ጨነቀው!
የተንኮለኞኦች አለቃ በአልኮሆል ተተብቶ
ይቅርታን ከወንበር አስነሳው ጎትቶ፣
እኛ ስንጠጣ ስንጨፍር በአንድነት
የምን ታዛቢ ነህ ከዚህ በመጎለት!
መጠጥ አትጠጣ ወይ ጭፈራው የለህ
እኛን ካልመሰልክ እዚህ ለምን መጣህ?
እያለ በመጮህ ምራቅ እየተፋ
አይኖቹን አፍጥቶ ፊቱን እያከፋ
አንድ ጠርሙስ ውስኪ ወዲያው ከፍቶ አመጣ
ከፊቱ ቀመና አለው አንካ ጠጣ
ይቅርታም ለመነው ተወኝ እኔ አልጠጣም
አላውቅም ጠጥቼ አሁን አልጀምርም፣
እኔ የምፈልገውን ይህው አግኝቻለሁ
ቁጭ ብየም ደስ ብሎኝ ነው እየተጫወትሁ።
እያለ ይቅርታ ማሳመን ቢሞክር
ጋባዦች በሙሉ ይሳሳቁ ጀመር
ለሰላሳ እየጠጣህ በእኛ ላይ ከምትስቅ
አሉና እጁን ያዙት ከእኛው ተደባለቅ!
ሁለት ተንኮለኞች ሁለት እጁን ያዙት
የሚሆነውን ሲያዩ ዕምነቱን ሊያስክዱት
እምቢ ያለውን አልኮሆል ሊግቱት አመጡ
እየተፉ እስጠጥሩት እየቀጠቀጡ
ሆና የኖረ ሰው አልኮሆል የማይወድ
ይሳሳቁ ነበር አእምሮ ሲከድ
በጣም ሲበዛበት መሬት ላይ ወደቀ
መተንፈስ ከበደው በጣምም ተጨነቀ፣
ያኔ ቶሎ ብለው ጎትተው አወጡት
ሰው እንዲሳለቅበት ከመንገድ ላይ ጣሉት።
የሆነው ሳያውቅ ሶስት ቀናት ቆይቶ
ምን ሆኜ ነው አለ ሐኪም ቤት ውስጥ ነቅቶ።
የሆነውን ሁሉ ቤተሰብ ሲነግሩት

ያስታውስ ጀመረ ምን እንዳደረጉት።
በደል ፈጻሚዎች በጣም ፈርተው ነበር
ሐኪም ቤት በድካም መግባቱ ሲነገር፣
ዘመድም ተነስቶ ሲሉት ልንከስ ነው፣
በሰፈሩት ቁና ለእያንዳንዱ ሰጭው
ፍርድ የማያዳግል ፍርድ የእግዚአብሔር ነው፣
እነሱን ከሰሸ ፍርድ ቤት አልቀምም
እምላኪ ብርቱ ነው ይከፍላል ሁሉንም።
ከይቅርታ እንደበት ይህንን ሲሰሙ
ተንኮለኞች ሁሉ በጣም ተገረሙ፣
ግን እሱም ቢተወው ሕግ ጠየቃቸው
ቅጣቱም አገኙ የማይረሳቸው።
በቅጣት ላይ ሆነው ይቅርታ ጠየቁ
የትላንቱን ጥፋት ዛሬ ስላወቁ
ቂም ይዞ ለበቀል ከንቱ ከመራወጥ
ይቅርታን ማስቀደም ይሆናል የሚበልጥ
እስቲ ቆም ብለን ወደ ኋላ እናስብ
ስንቶቹ ሰርተናል ጥፋት ያለገደብ፣
ሁሉን ይቅር ብሎ ከዚህ ያደረሰን
ከቶ እንዳይረሳ የአምላክ ውለታውን።

## • አይ ሥልጣኔ!

በጥንት ዘመናት ሰዎች የሚግባቡት
ነበር በምልክት ቃል በሌው ጩኸት
በጣም ጥበበኛው የሰው ጭንቅላት
እንዲያ ሁኔታዎች ባልፈቀዱበት
ሰዎችን አስችሏል ዘዴ እንዲማሩ
ለመግባቢያ የሚሆን ቋንቋ እንዲፈትሩ
ከንቱ ጩኸት ቀርቶ እንዲነጋገሩ፣
የሚሉትን እውቀው እንዲከባበሩ
እየቀየ ሲሄድ ሰዎም ሲሠለጥን
በወረቀት መላክ ሥሎ ምልክትን
ትርጉሙን በቀላሉ እንብቦ ማወቅን
በያሉበት ሆነው ቻሉ መግባባትን።
ምልክቱ እንሶ ተሰርቶለት ቅርጽ
ለዚያም ለምልክት ፈጠሩለት ድምጽ





ድምጽ ያለው ምልክት ፊደል የሚባለው
አየ ስልጣኔ ስንቱን ገላገለው!
በስርአት መናገር መጻፍ ሲዳብር
እየሰፋ መጣ የእውቀት መግቢያው በር፡፡
የመግባቢያ አይነቱም በጣሙን ዳበረ
ቴሌግራም ብሎ መልእክት ተጀመረ
ኋላም ባለሽቦ እውቀቱ ዳበረ
የሰው መጠያየቅ በስልክ ጠነከረ፡፡
የፊደል ክፍያ ቴሌግራም ቀረ
ከዚያም ተሻሽሎ የበለጠ መጣና
መልእክት ተጀመረ የሚሄድ በአንቴና
ማዞሪያውም ሆነ ሳተላይት ደመና
ቴሌክስና ፋክስም እንዲሁ ታከለ
በስልክ መስመር ላይ መጻፍ ተጀመረ፡፡
ስልጣኔ ገፍቶ ጨመረ ቴሌፋክስ
በስልክ ደብዳቤን ገልብጦ የሚያደርስ፡፡
አሁን ተጀምሯል በስልክ መተያየት
ስለተፈጠረ ኮምፒዩተር የሚሉት፡፡
ሰው ይፈላሰፋል ይለፋል ይሰራል
መሰልጠን ገደብ የለው መጭውን ማን ያውቃል፡፡

## ♦ አይጣልባችሁ

ነበር አንድ ሰው
ጓደኛው ተብዬ ያስቸገረው
ታሪኩን ሲያጫውት
ይገርማል ላልደረሰበት፡፡
ያየው ግን ይረዳዋል
የሰማም ይቀለዋል፡፡
የመሰለው ያወቀ
በጥበብ የረቀቀ
ግን የሆነ ባዶ
የሚኖር በተለምዶ
ከራሱ በቀር
የማይቀበል ምክር
መመከርን የሚንቅ
በታታሪ ላይ የሚሳለቅ
የማያውቅ እሸን
የማይወድ ማስረዳት
የሚቀለው መቆጣት

--- አይጣልባችሁ::
ሲናገር በጩኸት
የሚያደርቅ በድርቀት
ሁልጊዜ የሚል
እኔ ብቻ ነኝ ትክክል
ሲያጎርሱት የሚናከስ
ሲተውት የሚያለቅስ
ወዶ የሚወርድ
ከአልጋ ሲሉት እመድ
--- አይጣልባችሁ::
የሚቀርብ ሲርቁት
የሚፋጅ ሲቀርቡት
ፀባዩ ምስቅልቅል
አበሳጭቶ የሚገድል!
የተናገረውን የሚክድ
የሚያናድድ በግድ
ተናግሮ የልቡን
አበሳጭቶ ሌላውን
በደስታ የሚፈነድቅ
ወዳጁን የማያውቅ
--- አይጣልባችሁ::
ከሩቅ ሲያውቁት
ለዋዳጅነት የሚመኙት
ቀርበው ግን ሲያዩት
የሚፋጅ እንደ እሳት
ጸባዩ እንደ ጊንጥ
ጊዜ የማይሰጥ
ተናግሯ የማያባራ
በሌላው ስራ
ራሱን የሚያስጠራ
ምንም ቢሰጠው
ይሉኝታ የሌለው
--- አይጣልባችሁ::
የማያይ ጥፋቱን
የሚያጋንን የሌላውን
ከማውራት በስተቀር
ምስጢር የማይቋጥር
በክፋት የጠና
በቅንአት የሚያጣ ጤና
የተጠናወተው ምቀኝነት
ተንኮል ቤቱን የሰራበት





በማያውቀው ነገር
ድርቅ ብሎ የሚቀር
የማያውቅ ከቅሌት በቀር
--- አይጣልባችሁ::
ሳይጠጣ የሚመስል ጤነኛ
ትንሽ ሲቀምስ ነገረኛ
በሌሎች ፊት
ትልቅ መስሎ ለመታየት
ከመዋሸት የማይታክት
ወሬ የሚያካብት
ሳይኖረው ከራሱ
ወይ ከኪሱ!
ሲያድግ የሚኛ
በሌሎች ትከሻ
አዝነው ሲረዱት
እንደ ግዴታ ቆጥሮት
ትንሽ ሲቀርበት
የሚሆን ጠላት
የማልቀስ ያክል አዝኖ
ተቸገርሁ ብሎ ተማጽኖ
ተጥመዝምዞ እንዲረዱት
ይሁን ብለው ሲሰጡት
ለምስጋና ጊዜም የሌለው
ወደ መጠጥ የሚሮጠው
አለው እንዲባልም በሌላው
ድርቅ የሚል ካልጋበዝኩ ብሎ
የሚኖር ጓደኛውን ደልሎ
--- አይጣልባችሁ::
እንደ እስስት የሚለዋወጥ
እንደ ሳሙና የሚያዳልጥ
ያልሆነውን የሆነ
ለእውነት የመከነ
ከአንገት በላይ የሚስቅ
ምስጋና የማያውቅ
--- አይጣልባችሁ::
በችግር ጊዜ ረድተውት
ቆይቶ ትንሽ ሲያልፍለት
አላውቃችሁም የሚል
የፈረንጅ ፈረንጅ የሚሆን
ኪሳችሁን ብቻ አይቶ የሚቀርብ
ስታጡ የሚጭር ጠብ

--- አይጣልባችሁ።
ሲያከብሩት የማይከበር
የማይመልስ በጎ ነገር
ሰው የነገረውን ይዞ
ከዚያ ውስጥ አንድ መዞ
የሰራሁት እኔ ነኝ
የሚል አዋቂ እንዲሰኝ
በሌላው ሙያ የሚከራከር
በማያውቀው የሚያስቸግር
ለጓደኝነት የማይመች
በነገር የሚያስለች
ተናግሮ የማያባራ

የሚያማ ስም እየጠራ!
ለነገ የማይል ሲናገር
አንጎል የሚያዞር
--- አይጣልባችሁ።
የራሱን ጥፋት ለመሸፈን
ሌላውን ከማማት የማይቦዝን
እውነት ስሙ የጠፋበት
ውሸት ቤቱን የሰራበት
ወጁን በልቶ የሚያስበላ
የነገር ቡችላ

--- አይጣልባችሁ።

## ♦ ሰው የሚንቅ ሰው

ውርደት--- የሚጀምረው

ወድቀትም --- የሚከተለው

ከውጭ ሳይሆን --- ከራስ ነው።

ምስጢሩማ... ለገባው

አምላክ በራሱ የሰራው

መድኃኒት ነው ሰው ለሰው።

ሰውን የሚንቅ --- ሰው

ሰውነት በስጡ የሚጎለው





መፍትሄው ወንጌል ነው።

በጎ መስራት ደስ እንዲለው

የነገ ተስፋ እንዲናፍቀው

እግዚአብሔር --- ይዳሰው።

ሰውን አክብሮም መኖር

ለራስም --- ክብር፡

ሰውን የሚንቅ -- ሰው

ፈጣሪውን --- ከሀዲ ነው፡

አቅም በቻለው መርዳት

ለሰው አክብሮት መስጠት

ደስ ያሰኛል --- ተግባሩ

ተሳስቶ --- ቢያድሩ!

ሰው ከትውልድ አገሩ ተሰዶ

እየኖረ በውዴታ ተዋርዶ

እንደመኖር ተረዳድቶ ተዋዶ

ሲገባ ኑሮን ለማሸነፍ መጣጣር

አንድ እንደመሆን በችግር

አቃቂር ማውጣት ለሁሉ

በንቀት --- ማጣጣሉ

ሰው ባልዋለበት ማዋሉ

መፍትሄ አይሆን ለራስ ጣጣ

ጨዳራን ልጦ ጭንቅላት ነው የሚያሳጣ።

## ♦ የአውሮፕላን ተ ጉዞ

ፍተሻ አብቅቶ ተጭኖ ሁሉ ዕቃ
መንገደኛ ገብቶ ተሳፍሮ እንዳበቃ

ኑሮውን ሊገፋ ስራ ፈልጎ
ዘር ቆጠራን ምረኩዙ አድርጎ
በወግ አጥባቂነት እንደከረረ
በአጋጣሚ ስራ ጀመረ
የቤት እመል ይወጣል
ገብያ አብሮ ይውላል
ሰውየው ቀጣሪ አስመረረ
ስራ ሲያማርጥ ተባረረ።
ወጭው በዛ ተበደረ
አሁን ምን ይዋጠው
እንዲህ ነበርሁ ማለቱ አላዋጣው!
አይ! ኩምሽሽ አለ
ሆነ - - - እንደሌለ
ተኮማተረ- - - አነሰ
ሃሞቱ - - - ፈሰሰ።
አይ - - - ወኔ
ባለ አጥንቱ ወገኔ
ያለፈው አልፏል
ለሚመጣው መጠንከር ይበልጣል።
አቶ -- ስደት
ሌላ -- ህይወት
ዲፕሎማ የለ ዘር
ባዶ --- አስቀር!
ለክፉ - - - ያልተዘጋጀን
የሚያናውጥ - - - አእምሮን
ዘር - - - መቁጠሩ
በስም- - - መከበሩ
ሁሉም - - - ቀረ
ሆዱን - - - ጫረ
እንጀራ - - - ፈለገ
እንዲሠራ - - - ተዳረገ
ያገኘው ሥራ ሽንት ቤት ጠርጎ ማደር
የምን - - - መግደርደር
ጠም - - - ከማደር!
ሥራ - - - ክቡር ነው
በዕነት - - - ለገባው
ገንዘብ አይሸትም ለማለት
ፕኩኛ ነን አሌት
የላቲን - - - ተረት





አይናገርም - - - አመጣጡን
አያውቅም - - - ከፋዩን።
አይ- - - ወኔ
ባለ አጥንቱ ወገኔ
ገንዘብ አግኝቶ ሞቶ
ከራባት - - - ደርቶ
ቡና ቤት - - - ሲገባ
በጠራጊነቱ - - - እየባባ
የቆነጠጡት- - - ይመስል
የቆጥ የባጡን ሲቀባጥር
ትን የሚያሰኝ አጥንት ሲቆጥር
አሁንም- - - ያገረሸበት
ስደት - - - ያልሆነለት
የጠጣበትን አውጥቶ ለመክፈል
ገንዘቡ የሚያጋልጠው ይመስል
እጁን ከቶ የሚያነሰላስል
ስደት - - - ያልሆነለት
መልሱ - - - የጠፋበት
ይህን ምን- - - ትሉት?

## ◆ ድርሻህን ተወጣ

አንዱ ስለሌላው በቅን ማሰብ ቢችል
ድክመቱን ከማጉላት ከወሬ ቢገለል
ፈቃደኛ ቢሆን ሌላውን ለመርዳት
መራራቅ ርቆ በቀረበ አንድነት!
ዘርና ሃይማኖት ጎሳን እየጠሩ
የሚበጅ ነገር አንድ እንኳን ሳይሰሩ
ይባስ ማበላሸት የህብረትን ኑሮ
ይህማ ነበር ከጥንትም ጀምሮ።
ችግሩን ለመፍታት ማጻመጥ ነው ሕዝቡን
ጋሬጣማ ሞልቷል የሚነካ ቁስሉን።
ተራ ወሬ ይዞ በከንቱ ቢሮጡ
ወሬ ቢተርኩ የቆጡን የባጡ
መፍትሄ አይሆንም ለሀገር ለጎሳ
በብርታት መስራት ነው አገር የሚያነሳ።
አንዱ ትውልድ አልፎ ሌላም ሲተካ
የመስራት ቁምነገር እንዳይዘነጋ!

ለአያያዝ ይቀላል በዚሁ እመጣለሁ
ፌስታል ሌላም ነገር ልምን እይዛለሁ፣
አለና በውስጡ አሳመነ ራሱን
ልቡ መርጡዋልና ሳምሶናይት መያዙን።
ሳምሶናይቱን ይዞ ተንስቶ ተጓዘ
ወደ ሱቅ ሲገባም መግዣ ጋሪ አልያዘ፣
የሚፈልገውን በሳምሶናይት ከቶ
ሄዶ ተሰለፈ ነበር ሰውም በዝቶ።
የ እርሱ ተራ ሲደረስ ሳምሶናይቱን ገፋ
ሊከፍተው አልቻለም ቢለፋ ቢለፋ
ውስጡን አሳይ ሲሊት አለ ኮዱ ጠፋ!
ገንዘብ ተቀባዩዋ ጮኸች በቋንቋ ዋ
በአስቸኳይ ተጠርቶ መጣ አለቃዋ።
በእንግሊዝኛ አለው ምንድነው ችግሩ
ይቅርታ ገታየ ጠፋብኝ ኮድ ቁጥሩ፣
በማለት መለሰ ልብ እየጠመቀው
ከኋላው ያለው ሰልፍ ሲጮክ እየሰማው።
ከዚያም ተያይዘው ሄዱ ወደ ቢሮ
ዕቃውን አወጡት ሳምሶናይት ተሰብሮ፣
ባለ ሱቁም አለ እጠራለሁ ፖሊስ
አትሄድም እንዲሁ አለብህ መከሰስ
ለመስረቅ ነ እንጅ ይህን ያደረከው
መግዣ ጋሪ ትተህ ሳምሶናይት የያዝከው!
እንግዳው ለመነ እባክዎ ይማሩኝ
አዲሱዋ ሳምሶናይት እንደው ብርቅ ሆናብኝ
በ እርሱዋ ውስጥ ጨመርኩት ሌላው ሳይዞርልኝ
ለመስረቅ አይደለም በዘሬም የለብኝ።
በጣም ተጨዋጨዋኩ መጣ ገላጋይ
ባለሱቁም አለ ሂድ ፊትህን አልይ!
እሽ ብሎ ሮጠ ሌላ ጉድ ሳያይ።
ለመታየት ሲሻ ሰው ሰለጥንኩ ብሎ
ቤቱን ይመለሳል በሃፍረት ተጠቅሎ!
የስልጣኔ ጣዕም ምስጥሩ ሲገባ ነው
ወደ ላይ ከፍ ሲሉ ሳይሆን እተላው!





ገንዘብ አለብ ብሎ ቢገዛ የታየው
ችግር ከፈጠረ የታል ጠቀሜታው?
አባቶች ይላሉ ከመዋጥ ማላመጥ
ቢቀድም ይሻላል ከመናገር ማድመጥ
ለመሆን ሲሞክር ሰው ያልሆነውን
በህፍረት ይወድቃል ጠልፎ ራሱን!
እንደ ለመፈጸም እሰብ ሁለት ጊዜ
ይዩይልኝ ሥራ ይወልዳል ትካዜ!

## ♦ የቁንጫና ትኋን ታሪክ



ችግር በአሸነፈው በአንድ የድሃ ቤት
ቁንጫና ትኋን ሲኖሩ በአንድነት
ምክንያት ደርድረው አንድ ቀን ተጣሉ
መከባበር ቀርቶ አንች ተባባሉ።
የጠቡ መነሻ እንደዚህ ነበረ
ቂሙ የቆየ ነው የዋለ የአደረ።
አንድ ቀን ሰውየው ደክሞ ውሎ መጣ
ልብሱን አወላልቆ ከእንጨት አልጋው ወጣ
ወይዘሮ ቁንጫ ከደስታዋ ብዛት
ዘላ ወጣችበት በመስራት አክሮባት።
ወይዘሮ ትኋንም በጣም ተናደደች
ከምሽጓ ወጥታ ገና እየተሳበች፣
አብረን ተመግበን እንደዚህ ተራበች
ብላ በመገረም ልብቻ እያሰበች፣
ሰውየውም ሳይተኛ ገና እንቅልፍ ሳይወስደው
ቁንጫ ጀርውን ስትቆነጥጠው
ሰውየው ተነሳ በጣም በመናደድ
በተባይ ምክንያት ከቤቴ ልሰደድ?
ቆይ ይንጋ ብቻ ይህ አይደገምም
ተባይ ወይም እኔ አብረን ግን አንኖርም።

## ◆ ስጡኝ ብቻ የሚያውቅ

ሰውንስ ... አየሁት
አምኘም ... ቀረብኩት
የአቅሜን ረዳሁት
በፈቃዴ ስላደረግኩት
ውለታ አልጠየቅሁት
መስሉኝ ጥሩ ሰው
ቁምነገረኛ ግን የቸገረው
ቆይቶ ግን
ሲያወልቀው ማስኩን
አየሁት መልኩን፡፡
ሲደክም አቅሜ
ስወድቅ በቁሜ
ግድ አልሰጠው
ሆዱ ብቻ ታየው
እኔ በማጣቴ
ሳልሰስት በመቅረቴ
የምሩን አኩርፎ
ሄደ አልፎ
በጣም ያሳዝናል
ምን ገጠመው ሳይል
የጡት አባቱ የሆንኩ ይመስል
ግዴታ ሳይኖርብኝ
መልካም መስሎኝ
በተባበርኩ ወድጀ
ጠላት አፈራሁ በገንዛ እጀ
ለሁሉ ሳዳርስ
ለራሴ ሳለብስ
እኔ እየወረድኩ
ከፍ ባደረግኩ
ምስጋናው ቀርቶ
ቀረበ የጎደለው ጎልቶ፡፡
ይባስ ብሎ
በእኔ ላይ ዘሎ
ከላይ ለመጨበጥ
ያለአቅሙ የሚያጋጥጥ
እንዲህ ዓይነት ወዳጅ
ለምንም የማይበጅ





ነው የገጠመኝ
ሎተሪ አልወጣልኝ!
አቅመ በቻለው
ሁኔታ በፈቀደው
ሰውን መተባበር
መድረስ ለችግር
በጎ ተግባባር ነበር
ይሉኝታውን የሸጠ
በጥቅሙ የለወጠ
በስጡኝ የሚያስጨንቅ
እንኩ የማያውቅ
ብልጥ የሆነ የሚመስለው
የሌላው ባህሪ ያልገባው
አውሮፓ አሜሪካ ያልለወጠው
ስጡኝ የተጠናወተው
እንዲህ ዓይነት ዜጋ
ጭንቅላቱ የተዘጋ
አርቆ ለማየት
አእምሮው ወንፊት የሆነበት
የሰለጠነው ዓለም
ያለቀየረው ምንም
በውሸት የተካነ
ለእውነት የመከነ
ኧረ ስንት አለ
የሚኖር እየደለለ!

## ◆ አባይ

ርዝመቱን አይተው ሊፈልጉ ምንጩን
የአባይ መነሻውን ከጣና አንድነቱን
መጡ ከውጭ አገር ካሜራዎች ታጥቀው
ሄዱ ገሰገሱ መነሻው ግሼ ነው፡፡
ውጭም አወጡና በየሃገራቸው
በጣም ያስደንቃል ዓባይን ስናየው
ሆኖም ዜጎቻቸው በአገሪቱ ያሉ
ስለጥቅሙ አያውቁም ሲሉ ተማማሉ፡፡
በዓለም የታወቀው ተብሎ እንኳን ቢጠራ
ምን ጥቅም ይሰጣል በእርሱ ካልተሰራ ?
የግብጽ ሕይወት ነው የሚባለው ዓባይ
ብዙ ገባር ወንዞች የሆኑት አቀባይ
በዝናም ረዳት አፈሩን ጠራርጎ
ይወጣል ከአገር አገር አጥለቅልቆ

## ♦ ሥነ ምግባር

መልካም እየሰራ ከሰው ጋር የሚኖር
እንደራሱ የሚቆጥር የሌላውን ችግር
ችግሩን ለመፍታት በጣሙን የሚጥር
የታደለ ሰው ነው ትልቅ ስነምግባር።
በሌላው የማይቀና የሚኮራ በስራው
ይህን የመሰለ ስንት አለ በጎ ሰው!
ሰው ይደጋገፍ አንዱ ለአንዱ ያስብ
ከመጎተት ይልቅ ወደታች ከመሳብ
ድክመትን ማካረር ይቅር ስም ማጥፋቱ
ስንት ጉድ ሸፍኖ ሁሉ በየቤቱ !
ጥሩውን እናስብ እሰቲ እንረዳዳ
መጠላለፍ ይቅር ከቶ አኳኳን ባዕዳ!
አንዱ በጎ ሊያደርግ ከልቡ ሲነሳ
ማንኳሰስ ምንድን ነው መፈለግ ጠባሳ?
እኔ አልቻልሁም ብሎ ሌላውን ማጣጣል
ሁሉ ባዶ ቢቀር ለማንስ ይጠቅማል?
አንዱ ያልቻለውን ሌላው ሲሳካለት
ምቀኝነት ይቅር ጠሳት አድርጎ ማየት።

## ♦ የጋራ ምክር

ራስህን --- ለመገምገም
ከሌላው --- ቅደም።
አትምከን --- ለእውነት
ልብህ አይደንድን በውሸት!
ስህተትህን --- ላለመቀበል
ራስህን --- አታግልል።
የማታውቀውን በመናገር
እስብ --- እንዳታፍር።
ዕምነት --- የግል ነው
አገር --- የጋራ ነው
ፈጣሪም አንድ ነው።
ሌላው --- ያለፍላጉቱ
ወደ አንተ እንዲቀየር እመነቱ
ጭንቅላት አታዙር
ያለ ሰው እንዳትቀር።





ሌላው እንዲከተልህ ከፈለግህ
በእግባብ መኖር አለብህ።
ከመቸገር ተናግረህ ለማሳመን
በኑሮህ አሳይ ውጤቱን።
የእኔ --- ምክር
ይኑርህ ፍርሃተ --- እግዚ አብሔር
በመፈለግ ከንቱ --- ክብር
የማይሆን ነገር - - አትፍጠር፤
እንደ ችሎታህ --- ኑር።
ለቤተሰብ ደህና ሕይወት
ለሕዝብህ --- ደህንነት
ለሀገርህ --- ኩራት
ይኑርህ --- ምኞት።

## ♦ መጠጥ የማይፈታው

ሰው መግቢያ ሲጠፋው በዝቶበት ጭንቀት
ብዙ ተፍጨርጭሮ ኑሮ እምቢ ብሎት፤
ትምህርት፥ ስራ ዘመድ አልረዳ ሲሉት
ታሞ አልጋ ላይ ሳይውል ሲከብደው ሕይወት
ፍለጋ ይገባል ለመንፈሱ እረፍት።
መፍትሄ ነው ብሎ የሚጀምረው
እንደ ሰው ባህሪይ ሁሉ ልዩ ነው
የአንድ ሰው ታሪክ ነው አሁን የሰፈረው።
ስካርን ጀመሮ በገፍ መጠጣት
ሙዚቃ እያጮከ ቀንስ እስኪሉት
ሰውን እየዘለፈ ያለነበረ በፊት
አፍ እላፊው ሁሉ የሚናገረው
ዘመድ ጎረቤቱን የበጠበጠው
ተኝቶ ሲነሳ ጭራሽ ትዝ አይለው።
መረበሽ እንዲያቆም ሰው ሲጠይቀው
እንኳንስ እሽ ሊል ይቀድማል ቁጣው።
ይህችን የሰማትን በአእምሮው ይይዝና
ትንሽ መሽት ሲል አንድ ሲቀምስ ገና
ሆድ ያባውን ብቅል ያወጣዋልና
እየተንገዳገደ ወደ ቤቱ ሲሄድ
ስድቡን ይቀጥላል ወዳጅ የለ ዘመድ።
ምክር አልመለሰው አእምሮውን ሸፍኖ
በአመነጨው ሃሳብ በራሱ ተክኖ።
መጠጡ ሳይበቃው ዛሬንም ቀጠለ

ወረደ ወደ ታች ራሱን በደለ
ጭራሽ ጨመረበት ሃሽሽ ጠቀለለ።

## ♦ እግዚአብሔር ደስታ ነው

በእግዜር በመታመን በቀና ሲኖሩ
ተንኮል ቅንአት ትቶ ሲቆሙ ለክብሩ
በጎን ተወዳጅቶ ክፉውን ሲርቁ
ሕይወት አምላክ ብቻ መሆኑንም ሲያውቁ
በደስታ ተሞልቶ ይቀላል ችግር
ቦታውን ይወስዳል የእግዚአብሔር ክብር
ሰው ልቡ ሲሰበር በዕምነት በጸሎት
ግብዝነት ቀርቶ ሲኖረው ሕይወት
በኑሮው ሲተጋ ሳይመኝ ከሌላው
መስገብገቡም ሲቀር እያለ ሳይኖተው
አግኝቶ ይኖራል የመንፈስን ደስታ
መጨንቅ አይኖርም ጠዋት እስከ ማታ፣
የዘላለም ሕይወት ሲገባ ምስጢሩ
መጽሐፍ እንደሚያዘው በቃሉ ሲኖሩ
መልከስከሱም ቀርቶ ማበላሸት ሥጋን
በሕይወት ሲጓዙ መርጦ ቅድስናን
በመንፈስ ይኖራል በነጻ በክብር
የጸዳ ነውና መቅደሱ የእግዚአብሔር።
የሰሩትን ኃጢዓት ማንሳት መጣል ቀርቶ
ንስሃ ሲገቡ በፊቱ ተደፍቶ
ዘግይቻለሁ ሳይሉ ደጅ ቢጠኑት
እርሱም ዘንበል ይላል ጩኸት ለመስማት።
ያነሳል ከትቢያ ያለብሰል ክብር
ደስታም በዚያ አለ ነጻነት ጭምር።
ለአምላክ እየተው በሌላው ሳይፈርዱ
ቂም መያዝን ትቶ ሁሉንም ሲወዱ
ዕውነተኛ ኑሮ ለመኖር ሲጥሩ
እምነት ተስፋ ፍቅር መውስጡ ሲኖሩ
መነሳት ይኖራል በእግዚአብሔር ክብር
ይህም ዘላቂ ነው ዘለአለም ይከበር።
ምስጋና ቢስ ሆኖ ሰው በራሱ ቢወድቅ
ሰው በእብሪት ከኖረ አምላክ አይጠየቅ
ሁሉም ያለው መስሎት ከአምላኩ የራቀ





ይህ ደካማ ነው ቆሞ የወደቀ!
ያለውም ተወሰደ ደስታ ያጣልና
ሰው ፈጣሪ አይርሳ ያቅርብ ምሥጋና።

" እነሆ የእግዚአብሔር እጅ ከማዳን አላጠረችም ጆሮ ውም ከመስማት አላቋረጠችም ነገር ግን በደላችሁ በእናንተና በአምላካችሁ መካከል ለይታለች፤ እንዳ ይሰማም ኃጢዓታችሁ ፊቱን ከእናንተ ሰውሮታል።"
( ት/ኢሳያስ 59:1-2)

ርሃብ ሲታገስ የሰላም ድህነት!
በአስራ ሰባት አመታት ደርጉም ወደቀና
ቀጥሎ በመጣው ብዙም ሳይቆይ ገና
መፋጀት ጀመረ ሰው ጎሳ ለየና::
ተስፋና ሕይወቱ ብሎ ከአደገባት
ሰው ተገደደ ለውስጥ ለውጭ ስደት
አውሮጳ አሜሪካ በአገሩ ሲኮራ
ችግረኛ ሲለን አገር እየጠራ
እስከ መቸ እንኑር ስማችን ተቀይሮ
የዳቦ ቅርጫቶች አልነበርንም ድሮ?
አለንሽ እንበላት ይህችን የተሰፋ አገር
ሆዳችንም ጠግቦ በሰላም እንደር።

## ◆ በምላሱ ራቀ

አቅሙ ምላስ ሆኖ በአፉ የከበረ
ጉልበት አለኝ ብሎ ሲመካ ኖረ
ምንም ያለሆነውን እየቀባጠረ
ፈጥሮ እያወራ አንጀት ያሳረረ
ባእድ ዘመድ ሁሉ በቁም ያሰመረረ
ምላሱ የሚባል አንድ ሰው ነበረ::
የሰው ሃብት ሲቀማ እድሜ አልጨመረ
ለብቻው ሲያከማች ሰው ጠም አሳደረ::
አፉንም ሲከፍተው ጥርስ አለው ምላሱ
ጉልበቱ እርሱ ነው በቃል መናከሱ!
ቃሎቹም መርዘኛ አእምሮ አቁሳይ
ምልክት የማይተው በዓይን የማይታይ::
ሰው ሊያድነው ጣረ መከረ ዘከረ
እንዴው ይባስ ብሎ በተንኮል ዳበረ::
በምላሱ ነገር እየሰረሰረ
ሰልጥኛለኩ እያለ ወደኋላ ቀረ
በምላሱ ራቀ ራሱን አሰረ::





## • ሰው በሰፈረበት ጽዋ ...



የመከኑ --- ለእውነት
የማይረዳቸው ምንም አይነት ታብሌት፡
ዘለው እየዋሹ የቆጡን የባጡ
የሚባሉትን የማያዳምጡ
በሃሰት ብቻ የነገሱ
እስከ አሁን ያሉ እያወሩ
ሁሉን ያስመረሩ
በሰላም የሚኖረውን የኖረውን
ነካክተው ቁስሉን
በሰው ስቃይ የሚደሰቱ
ምግባረ ጎደሎ ከጠዋቱ
ተንኮል ወዳጃቸው
ደግነት ጠላታቸው
አሉ በየቦታው::
ግን እኮ---
ሰው በሰፈረበት ---
መቀበሉ አይቀርለት!

## ◆ ሰው መድኃኒቱ ...

አንድ ሰው ደፍቶ አንገቱን
በችግር እየመራ ሕይወቱን
ቁለቁል ወርዶ
ለውድቀት ተገዶ
ባለበት ህይወት
ያፈራውን ጓደኝነት!
ዋጋ መስጠት
አያጠያይቅም አስፈላጊነቱ
ሰው ነው መድሃኒቱ::
በጎ ማድረግ
በማንም ሳይገደድ
ትልቅ ነገር ነው
ሁሉም ቢያውቀው::
ነገር ግን ቆይቶ
የሰራውን አስልቶ
ከጠበቀ ምስጋና
ይቀረዋል ገና!

በራሱ ፈቃደኝነት
በህሊናው መሰረት
ላደረገው በውዴታ
ምስጋና መጠበቅ ግዴታ
ተገቢ አይደለም
ሞራል አይሆንም !
ይህን ከሰራኩ
ያንን ከአገዝኩ
ስጦታ ወይንም ምስጋና
የሚያስከብ እንደ ጀግና
ማግኘት አሰለብኝ
ሰው እንዲያውቀኝ!
የዚህ አይነት ህልም
ለማንም አይጠቅምም
በግል ህይወት
ሲኖሩ በጓደኝነት
የወገን ስቃይ
ቀድሞ ሲታይ
መመስግን የሚለው ስሜት
ይጠፋል ከአንደበት
በሌላ በኩል
ነውና ባሕል
አንድ ግለሰብ
መቸገሩን ሲያስብ
ብቻውን ሞክሮ
ብዙ ጥሮ ግሮ
መፍትሄ ሲያጣለት
የችግር ህይወት
ጓደኛው ደሶለት
ሲረዳው በበፈቃደኝነት
ሌላው  ይቅር
መጠጥ ዝክር
በባህላችን መሰረት
ማመስገን አለበት::
አግባብ ያለው ይሉኝታ
ነው የባህ ገጽታ::
እንዲሁም ---
የአንድ ሰው ፈቃደኝነት
ለሀገር ለወገን መስራት
ከተያያዘ ከግል ጥቅም
ምስጋና አይመልሰውም::





ይህኛውም ቢሆን
የግል ጥረቱን
ለሀገር መድከሙን
ውለታ እንዲያዝለት
ቁንጮ እንዲያደርጉት
ከሆነ የሚታክት
ይሉኝታ አያውቅም
አይከፋም ቢላጭም::

## ♦ ታላቅ ሀብት ጤንነት

ሰው ጤንነት ከአለው
ምንም ቦታ አይሰጠው
ሁሉም ትዝ የሚለው
ሲጠቃ ብቻ ነው::
ጤና ነው ትልቅ ሃብት
መጭውን ለማየት፤
ገንዘብ ቢትረፈረፍ ቢበዛ
ጤንነት ከሌለ ሕይወት አይገዛ!
ቀጠሮ እያበዙ ታሞ ከመማቀቅ
ኋላ ከመቆርቆር ከንቱ ከመጨነቅ
ለአንዲት ውድ ሕይወት
ቅድሚያ ይሰጥ ለጤንነት
ነውና ለሁሉም መሰረት::

## ♦ ዛሬም አልተማረ

ፈልግ ታገኛለህ ሌላ አለ ገነት
ሰው ሆኖ ሰው ማጣት
በቅን ተረዳድቶ ከመኖር በጋራ
በሆነ ባልሆነው መፍጠር ባላንጋራ
ሰው መሆን ምንድን ነው
ስራህን አስበህ ራስህን ጠይቀው
የትኛው ባህሪይ ነው ከአውሬ የሚለየው
ከጥንቱ ሲፈጠር ክቡር የከበረ
ከንስሳትም በላይ የሰው ልጅ ነበረ::
ማእረጉን ጥሎ በራሱ ያፈረ
ቃሉን በመስበሩ ገነት ወጥቶ ቀረ::

## ◆ የወሬ መቀስ

አሹሉ የወሬ  መቀስ
መራወጥ ስም ለማርከስ፤
በሌላው ሲቀስሩ እጣትን
መርሳት ውድቀትን
በሁለት ስለት መቁረጫ
ገብቶ ማጣት መውጫ
ያን ቀን መርገም
ዘግይቶ አይጠቅም፡፡
ጆሮ ለራሱ ባእዳ
ያላወቀ ባለእዳ
የደበቀው ከንዳ
በአደባባይ ሲወጣ
እርሱ ግን ሌላ ሲያመጣ
ሰው ጥርሱን ሲያሳየው
የሳቀለት እየመሰለው
ለወሬ የሚጣድፍ
የቆመ በትዝብት አፋፍ፤
ዘመድ ወዳጅ የማይመርጥ
በሃሜት መቀስ የሚቆራርጥ
ከዚህስ መራቅ ነው
ለራሱ ባእዳ ከሆነው፡፡



## ◆ በቀና መራመድ

ለተንኮል አለመገደድ
በቀና መራመድ
ባልተሰጠ ተግባር
ጥልቅ ብሎ አለመቸገር፡፡
ከመጻህ ይልቅ በጉልበት
ትንሽ ቆም ብሎ ማየት
ቀና ሲሉ ጣራ
ሲዞሩ ባላንጋራ
በፍላጎት ማፍራት
ይህ አይነት ህይወት
ቅኝት የበዛበት
ሰው ለምን ይፈልጋል?
ደግነት ይመረጣል፡፡





## ◆ ምግብ ብቻ አይበቃም



ምግብና መጠጥ ሁሉን አይመልሰው
ሰላም ለተጠማ ነገር ለሰለቸው!
ሰው መንፈሱ ሲራብ ፍትህን ሲጠማ
በእውን ሳይኖርበት ጆሮው እየሰማ
መንፈሱ አይረካ ምን ሆዱ ቢሞላ
በጦርነተ እሳት ሰላሙ ሲበላ፡፡
ምግብ ይኑር እንጅ ሞልቶ ተትረፍርፎ
ሰው እንዴት ይኖራል መንፈሱ ተገፎ!
ደስታን የመረጠ ሲኖር በድሎት
ፈተና እና ፈታኝ ማለፍ አለበት፡፡
ከሌሎች እንስሳት ሰው የሚለይበት
በሆዱ አይደለም አብስሎ በመብላት፥
ከዚህስ የላቀው ጥበብ መቻሉ ነው
መፍትሄ መፍጠሩ ማሰቡ ለመጭው፡፡
ምግብና መጠጥ ቢቀርብ በየአይነቱ
በዚህ መልስ አያገኝ የመንፍስ ጥማቱ፡፡

## ◆ የይሉኝታ ታሪክ

ሰው እንዳይቀየም ሲጎዳ ራሱን
ያለሆነ ሲነግሩት እያወቀ መልሱን
ከመሰላችሁስ እሽ ልቀበለው
ልዩ ነጥብ የለም እኔ የማሻሽለው
እያለ ሲስማማ እንዴው ልኑር ብሎ
አይኖሩ የሞኖር ራሱን አታሎ፤
አንድ ሰው ነበረ የሚባል ይሉኝታ
ለሌላው የሚሮጥ ጠዋትና ማታ፡፡
አንጀቱ እያረረ መልስ አይሰጥ ተጨንቆ
የማይረባ ነገር እያለፈ አድንቆ
አዎ! እሽ! ማለት የዘወትር ቃሉ
አሜን ብቻ እያለ ጥፋት አለማስተባበሉ
የማይቆረቁረው ይሉኝታ ማብዛቱ
ዛሬም ያው የሆነ ልክ እንደ ትላንቱ
ይሉኝታ መጠሪያው ይሉኝታ አባቱ
ሲወርድ ሲዋረድ ከወላጆች ወርሶ

ሌላው ቅር እንዳይለው ኑሮውን አኮስሶ
አእምሮና ኪሱን ለሌላው ሲቸር
ምስጋናም ላይደርሰው እድሜ ላይጨምር
መሳለቂያ ሲሆን በኑሮው ሲቀር
ይሉኝታ ነበረ እንዲህ የሚኖር::
ጨዋታ ጣእም ሲያጣ ሲሆን የማይመች
እጅ እጅ አለኝ ይላል ሰው ነገር ሲሰለች!
ይሉኝታ ሲበዛ ውጤቱ ጉዳት
ሰው ከአልተናገረ ሃሳቡን በእውነት::
ሰው ሆይ!
እሽታና እምቢታን በአግባቡ ተማር
በከንቱ ቃል ኪዳን እንዳትቸገር::
ስትወድቅ የሚያነሳህ ወደአንተ የሚዞር
ሰው ቶሎ አታገኝም ከአሁኑ ተማር::

◈ ◈ ◈

## ♦ የዘመኑ ቅኔ

መናገር ፈልጎ ጠፍቶት አባባሉ
ሊያስተናግድ ሲሻ ሰውን እንዳመሉ
አቅም ግን ተስኖት አልበቃ ለሁሉ!
የሞላው ሲጎድል መጥፎ ሰው ነው አሉ::
ኋላ ነው የገባው ሲያበላሸው ፈቱን
ከቶ መቸ አወቀ ፈጎ ጣጣ መሆኑን::
ሰላማዊ ነበር የሚኖር በግሉ
በቁሙ ገደሉት አምትተኛ እያሉ
ሐኪም ነው ጠበቃ መሀንዲስ ስትይው
አይ አለማወቅሽ ለካስሺ አዛኝ ነው።
የሚረሳ አይደለም ውሎ ስላደረ
ከቶ ለመሆኑ መናፈቅ መች ቀረ::
ሊታላቅ ቁምነገር ስታደርሽ ልጅሽን
መጠየቅ ጀመሩ አሉ ኮራብሽን?
ደብር እያደሩ ሲያጠኑ ቅስና
ለታቦር ደረሱ ትምህርቱ በቃና
ፈትል ጋቢ ለብሶ ሰፌር ያስቸገረ
ጠላምች ያላየ ባላገር ነበረ::
ዙፋን ሶፋ ሲሆን ሲቀየር ዘመኑ
የሚገዛው በዛ ሻሮች መነመኑ።





አዋኪ በሽታ እድሜው የረዘመ
ጤነኛ አካል ገብቶ ልብ አቀረዘመ::
ወርቅ ሚዳ አንጥፎ እጅዋን ሲለምናት
ድህነቷን መርጣ ዓመደው ተሻላት።

◈ ◈ ◈

## ♦ በኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ሐይማኖት በዓላት

1- ልደታ፥ ራጉኤል፥ ኤልያስ፥ ዮሐንስ
2- ታዲዮስ ና አባ ጎባ :
3- የበአታ በዓልና አቡነ ዜናማርቆስ
4- ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ
5- አቦ
6- ቁስቋምና ኢየሱስ
7- ስላሴም
8- አባ ኪሮስ
9- ቶማስ
10- መስቀለ ኢሱስ
11- ሃና ና ያሬድ
12- ሚካኤል
13- ሩፋኤልና እግዚአብሔርአብ
14- አቡነ አረጋዊ
15- ቂርቆስ፥ ጨርቆስ፥ገብረክርስቶስ
16- ኪዳነ ምሕረትን
17- ስጢፋኖስ
18- ዮስጣቲዮስና አርባእቱ እንስሳት
19- ገብርኤል
20- ህንፀተ ማሪያም
21- ማሪያም
22- ኡርኤል ፥ ጊዮርጊስ
23- ተክለሃይማኖትና ክርስቶስ-ሰምራ
24- ማርቆስና በአቡነ አቢብ
25- ዮሴፍ
26- ቶማስ ዘህንደኬም
27- መድኃኒአለም
28- አማኑኤል
29- በዓለ ወልደ በዓል
30- ማርቆስ
ለአንዱ በዓል ሆኖ ጎረቤት ከሰራ

በዚህ ቀን አይገባም ቡና እኳን ቢጠራ
ተንትነን ስናየው ሁሉን በየተራ
ፈተናው ብዙ ነው የሰው ልጅ መከራ
አደራ እባካችሁ እንዳንረሳ ሰዎች
አደራችን ፆጽና በሶስቱ ስላሶች፡፡
በእምነት አንበርታ ከሁሉ እንፈወስ
በር ግን እርሱ ነው እየሱስ ክርስቶስ።

## • የሃሜታ ቤተሰብ

አንድ ሰው ነበር ሃሜታ የሚሉት
ሲያነሱ ሲጥሉት በወሬ ሲመቱት
ብርታትን የሚያገኝ ሲሰዎች ሁሌ ሲያሙት፡፡
ይህ ግን ከቀረበት አይወስደውም እንቅልፍ
ሃሜተኛ ፍለጋ ያቋርጣል ጠረፍ
ከእለታት አንድ ቀን ቡና እየተጠጣ
አቶ ሃሜት ስንቁ ጨዋታ አመጣ፤
እንዴት ያሳዝናል አቶ ታማን  ብታዩት
ያለአቅሙ ሲሞክር ብልጦት ሞጩለፉት
ግን ደግ አደረጉ ደግሞ ምን አባቱ
ምን አቅለበለበው አያርፍም ከቤቱ
የሃሜት ወንድሙ ቀብል አደረገና
እርሱ ጉድ አለበት መች አያችሁ ገና!
ከዚች ከሚስቱ ጋር አብሮ ከቀጠለ
ራሱን ይስታል ሃሜት ይህን አለ፡፡
የአቶ ሃሜት ስንቁ እህቱም ቀጥላ
ሁሌ እንደዞረች ነው ስኒ ተከትላ
በጣም ትጠጣለች ነች ሰካራም
ሌላም ወንድ ይዛለች ትለዋለች ወንድም፡፡
እያለች  በሃሜታ ሃሜት አባባለች
ሃሜት የጠማውን ወንድሟን ለኮሰች፡፡
ሃሜት ተቃጠለ ይህንን ሲሰማ
መጣሁ ብሎ ወጣ ልደውል ለእማማ
የአቶ  ታማ ወንድም ፈረንጅ አገር ነዋሪው
የሚጨነቅለት በክፉም በደጉ አለሁህ የሚለው
ድሮ አገር ቤት ሳለ ሃሜታ ያውቀዋል
ጎረቤት ነበሩ ሲጫዎቱ አድገዋል፡፡
ስልክ ደወለና ሃሜት ሰላም ሲለው
ሃሜት እንደምን ነህ ዘመድስ ደህና ነው?
ብሎ የቆየውን ሰላምታውን ሰጥቶ





እንዴት ልትደውል ቻልክ ድምጽህ ነበር ጠፍቶ
እህህ --- ብሎ ሲናገር ሲቀጥል ሲቃጣው
ሃሜት አቋረጠው ቡጨቃ አስቸከለው፡፡
በሌለ ቤቴ ነው የምደውልልህ
መድሃኒት ፈልግለት ለዚህ ለወንድምህ፤
እንዴው ይመስለናል ያስደገመችበት
ሲጃጃል ይውላል እምቧ ሲል እንደከብት፤
ከተማው በሙሉ ወሬው ስለለእነርሱ
መካሪም አልቀረ ሽማግሌ ቄሱ፡፡
እንዲኖር ከፈለግህ ወንድምህ ህይወቱ
ማላቀቅ አለብህ ከዚች ከሴቲቱ፡፡
ሃሜት ተነፈሰ ቃጠሎው በረደ
ገባ በአድማጩ ውስጥ ጀመረ አነደደ፡፡
በጣም አመሰግናለሁ ስለደወልክልኝ
እኔም ጠርጥሬያለሁ ድመጹ ሲጠፋብኝ፡፡
ስልኩንም ዘጋና አሰበ በንዴት
እኔ እየደወልኩ በስራ ቀን ከሌት
እነርሱን ለመርዳት የምልከው ሁሉ
እሰከ አሁን መች አወቅኩ ለጥፋት መዋሉ!
አገር ቤት ደወለ ታማን አገኘው
እኔ ወንድምህ ነኝ ጤናህስ ደህና ነው?
በማለት ጠይቆ ከአንገት በላይ ብቻ
ችግር ላይ ነህ አሉ የጠፋለት መፍቻ
ከአንዴ ሁለት ሶስቴ ሰምቻለሁ ሁሉን
የምልከው ገንዘብ ለስካር መዋሉን!
ከዚያም ሰምቻለሁ በጣም ብዙ ነገር
ታዋቂም ሆናችሁ በስካር በመንደር፡፡
ይህን ኑሮ ከመረጥክ ራስህ ታውቃለህ
በሞቴ ምያለሁ ገንዘብ ላልክልህ፡፡
ታማ አልገባውም ወንድሙ የሚለው
እኔ መጠጥ ከአቆምኩ ዘመኑ ብዙ ነው
ከስንት አመት ወዲህ አልኮሆል የሚባል
የማልቀምስ መሆኑን ዘመድ ወዳጅ ያውቃል፡፡
አንተ እንደምታውቀው ከስንት አመት በፊት
ሰላም ሰው ደብድቤ በስካር ምክንያት
ያኔ ነው የማልኩት እስር ቤት እያለኩ
ሰው አትበሉኝ ብየ አልኮሆል ከቀመስኩ፡፡
እስከ ዛሬም አለሁ በዚሁ ጸንቻ
እውነቱ ይህ ነው አላውቅም ጠጥቼ፡፡
ወንድሙም ከውጡ ጫን ተነፈሰና
ብስጭቱ በርዶ እረግቶ እንደገና

ታማ የሚለውን ታሪኩን አድምጦ
በሞቱ መማሉን እያሰበ አፍጥጦ፤
እንደዚህ ከሆነ አንተ እንደምትለው
ሰው የነገረኝ ከየት አምጥቶ ነው?
ይጋነናል እንጅ ጫፍ አልባ አይወራ
እንዲሁ ተፈጥሮ ሰው ባልዋለው ስራ::
በማለት እውነቱን ሊያዋጣ ሞከረ
የወንድሙን ጠጭነት ስለጠረጠረ::
ታማ ቀጠለና ወንድሙን ጠየቀ
በሰማው ሁኔታ ስለደነገጠ::
ከቶ ለመሆኑ ማን ነው የነገረህ
ለስልክ የበቃከው እንደዚህ ተናደህ?
ወሬኛውን እርሳው አንተ ደህና ከሆንክ
ሁሉንም አትመን አይሆንም ዘመድህ::
ወሬውም አልወጣ አለፈ ሳምንቱ
ሃሜት ታማን ሊያየው ሄደ ወደቤቱ::
በአግባቡ ሰላምታ ለታማ ሳይሰጠው
የቸኮለበትን ጥያቄ አቀረበው
ምን ያክል እውነት ነው ሰው የሚያወራው
ትለቁ ወንድምህ ፈረጅ አገር ያለው
ከአንተ ጋር ተጣልቶ ሌላ ሊረዳ ነው::
የሚሉት ሰምቸ ልጠይቅህ መጣሁ
ስለማትሰማ ጓደኛህ ስለሆንሁ::
የታማ ጆሮዎች ያን ጊዜ ቀጥ አሉ
ገብቷቸው ነበረ ሃሜት ማታለሉ!
አቶ ሃሜት ስንቁ ጨዋታ ቀጠለ
እስከ አሁን የሰራው ከቶ አልበቃው አለ::
ማንን ነው የሚረዳ ብሎ ሲጠይቀው
ስሙን አላውቀውም አለና መለሰው::
እንዴው ለመሆኑ ለአንተ ማን ነገረክ
ያለኸው እኛ ጋር ውጭ አገር አይደለክ?
ሃሜት ግን ጭጭ አለ ምንም እንዳልሰማ
መቅለስለስ ጀመረ ክብር የለው ግርማ ::
ታማ ስለገባው እርሱ እንደደወለ
በስልክ ባይሆን ኖሮ ሰው እንዳጋደለ::
ሃሜት ለካ አንት ነህ ከሰው የነጠልከኝ
ዘመድና ወዳጅ ደስታ ያሳጣኸኝ፤
መጽደቅም ባትፈልግ ገሃነም ተሸሎህ
ሃሜታህ መርዝ ነው በህይወት እያለህ
በማለት ሲናገር ተለውጦ ፊቱ
ቢላዋ አወጣና አንተ ክፉ አንተ ከንቱ





አለና ሃሜትን ምላሱን ቆረጠው
አከታተለና ጆሮውንም ላፈው፤
ፖሊስ ጣቢያም ሄዶ ወንጀሉን አስረዳ
በሥጋም በነፍሱ ገባ ሌላ ዕዳ።
ሃሜት አከተመ ምላስ ስራ አቆመ
መናገር አልቻለም በቁሙ እያለመ።

## ◆ ድንግል ማርያም

እግዚአብሔር አስቀድሞ ሰማይ ምድርን ሰራ
አየርና ውሃ ፍጥረትን በተራ፤
ከጨረሰ በኋላ አዘጋጅቶ ሁሉን
እግዚአብሔር ፈጠረ በራሱ መልክ ሰውን::
ወንድና ሴት አድርጎ ፈጥሮ አስቀመጣቸው
ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉ ብሎ ባረካቸው::
የየብስ የውሃ እንስሳትን ሁሉ
በሰማይ በራሪ አእዋፍ ሳይቀሩ
ሁሉን እንዲገዙ ሰጣቸው ስልጣን
የሰው ልጅ እንዲኖር አልምቶ ምድርን::
ከአስረዳ በኋላ መልካምና ክፉውን
በኤደን ገነት ውስጥ አስቀመጠው ሰውን፤
አዳምና ሄዋን በገነት ሲኖሩ
ርቃና ነበሩ አይተፋፈሩ::
በእባብ ተመስሎ ሰይጣን የሰው ጠላት
ክልክሉንም ፍሬ አደረገ እንዲበሉት::
ከዚህም ጀምሮ ሰው ቃሉን ሰበረ
ከገነትም ወጣ በሾክ መሬት ኖረ።
አዳምና ሄዋን ሲወልዱ ሁለት
የአለም ሕዝብ ብዛት ነበር አራት
ሰይጣን አላረፈም ገባ በቃየል
በቅንአት ገደለ አቤል ወንድሙን ::
የሰው ልጅ በምድር ላይ ቆይቶ ሲባዛ
ፈጣሪውን ረስቶ ሆነ የማይገዛ።
ብዙ ትውልድ አየ እምላክም በትእግስት
ሰው አልተመለሰም ከተንኮል ከጥፋት::
ሰውን በመፍጠሩ ፈጣሪ አዘነ
ስለዚህ ሁሉንም ሊያጠፋ ወሰነ::
አካሄዱን ከእግዜር አብሮ ያጣመረ
አንድ ኖሕ የሚባል ጻዲቅ ሰው ነበረ::
እግዜር ተናገረ ከነቤተሰብህ ወደ መርከብ ግባ

በዚህ ትውልድ ፊት ጻዲቅ ሰው ነህና፤
ከእንሳስትም ሁሉ ከየአይነቱ አስገባ
ለዘር የሚከንህ ኋላ የሚራባ።
ከዚያም ውሃ ሙላት ዋጣት አለምን
ሰው የለ እንስሳ አጠፋ ሁሉን።
ውቅያኒስ በሳው ጠፋ ሳር ቅጠሉ
ስለ ሰው ጻዲቅነት ሰምንት ሰዎች ቀሩ
እግዚአብሔር ባረከ ስራቸውን ጭምር
በኖህ በአብርሃም ዘር ሞላች ይህች ምድር።
ሰው ግን አላቆመም ሃጢአት መስራቱን
ግድያ ብቀላ ጣኦት ማምለኩን፤
ፈጣሪ  አስነሳ ነቢዩ ሙሴን
ለአሕዛብ የሚገልጽ ቃለ እግዚአብሔርን።
ዘመናት አለፉ ሰውም ክፉ ሆነ
ፈጣሪ ተረስቶ ሰውም ክፉ ሆ፤
አምላክ ቸርነቱን ትእግሱን ሳይጨርስ
ሌላ ነቢይ ላከ ሰውን ለመመለስ፤
ለኢሳያስ ሰጠው እንደገና ትንእንቢት
ለሰው ልጅ በሙሉ የሚሆን ምልክት፥
ድንግልም ፅንሳ ወንድ ትወልዳለች
ስሙን አማኑኤል ብላ ትጠራለች።
የእግዚአብሔር መንፈስ ጥበብ ማዋስተዋል
አውቀትና ምክር መንፈሳዊ ሐይል
እንዳየው የማይፈርድ ሰምቶ የማይበይን
ለድሆች የዋሆች የሚሰራ በቅን
ጽድቅ መታጠቂያው ታማኝነት መቀነቱ
ሰውን ከሞት ማዳን የሆነ መልእክቱ
ይወለዳል ብሎ ቀድሞ ተናገረ
የፈጣሪ መንፈስ በማሪያም ላይ ኖረ፡
ታሪኩም በአጭሩ እንደዚህ ነበረ።
ወደ ድንግል ማሪያም በገሊላ መንደር
መላኩ ገብርኤል ተላከ ከእግዚአብሔር።
ፀጋ የሞላብሽ በጣም ደስ ይበልሽ
ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ፤
ብሎ የምስራች ሲነግራት ደንግጣ
ይህ አይነት ሰላምታ ከየት እንደመጣ
ግራ እንደተጋባች መልአኩ ገብቶት
ፀጋን የተሞላሺ አላት በእግዜር ፊት
እነሆ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ
ስሙንም አማኑኤል ብለሽ ትጠሪዋለሽ።
አምላክ የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል።





በያእቆብ ቤትም ላይ ለዘላለም ይነግሳል።
ቀጥላም ጠየቀች
ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል?
መልአኩ መልስ ሰጠ
መንፈስ ቅዱስ በአንች ላይ ይመጣል፤
ገብርኤል ሁሉንም ዘርዝሮ ሲያስረዳት
እንደቃልህ ብላ ተቀበለች በእመንት።
ጌታዬ መድሃኒቴን ነፍሴ ታከብራለች
መንፈሴም በአምላኬ ሃሴት ታደርጋለች
ትውልድ ሁሉ ይለኛል ብጽእት
ተመልክቷልና የባሪያይቱን ውርደት።
እርሱ ስላደረገ በእኔ ላይ ትልቅ ስራ
ቅዱስና መሃሪ እርሱን ለሚፈራ፤
ድንግል ማሪያም በመንፈስ ነበረች
በእህቷ ኤልሳቤጥ ፊት ይህን ተናገረች።
በመንፈስ ቅዱስ ሐይል ሕጻኑ ተፀነሰ
ጊዜውን ጠብቆ መውለጃዋ ደረሰ፤
ክርስቶስ ተወልደ በቤተልሄም ይሁዳ
በሙሉ ሊከፍል የሰውን ሁሉ እዳ።
በአካል በጥበብም አደገ በሞገስ
ስራውም ገነነ  ታወቀ ክርስቶስ
በመስቀል ላይ ዋለ ደሙን ለእኛ አፍስሶ
በእዳ እንዳይጠየቅ ሰው ተመልሶ።
ጻዲቅ ማሪያም ሆይ ምንጊዜም ብጽእት
ክብር ይገባሻል ምስጋና በእውነት፤
ለእኛ መዳን ሆነ የማሕፀንሽ ፍሬ
ከሞት ባያወጣን ማን ይኖራል ዛሬ።

## ◆ ከምልክት በላይ

ያለፈውን ስናይ ታሪክ ስናጠና
በጣም ጥቂት ሳሉ የሰው ልጆች ገና
ተብሎ ሳይታወቅ ስሙ ክርስትና
ነበሩ ነቢያት እግዜር ያስነሳቸው
እግዜአብሔር ሲሰራ ሆኖ በውስጣቸው
መንግስት የሚያናውጥ ነበረ ቃላቸው።
ለዚህም ምስጢሩ ድምጹን መስማት ነበር
ፈቃደኛ መሆን እግዜአብሔር ሲናገር፤
ሲልከው ለመላክ ወደ ሁሉም አገር።
የበአል ነቢያት እንዲያ በበዙበት

እርሷ የምትለብሰው እኔ ስለሌለኝ
ይህ ጉርብትና በጣሙን አስጠላኝ፤
ከመቸ ቆጥበው ይህን ቤት ሰሩ
የለንም ባዶ ነን እያሉ እያወሩ፤
ተሸለናል እያልን በካዲላክ ስንሄድ
በኪራይ ቤት ኖረን ሁሌ ድግስ ስንወድ
እነርሱ ቀደሙን በእግር እየሄዱ
መኪናውም ቆመ አለቀ መንገዱ።
ከምንበሳጭስ መላ እንፍጠርና
ቤት እናሸጣቸው እንዲቀሩ መና!
ብለው ይነሳሉ የቆመ ለመጣል
ሌላው ሲጎሳቆል የሚያድጉ ይመስል!
እንዲህ አይነት ፍጡር ከአራዊት የባሰ
በቤት በአደባአይ አለ እያፈረሰ።
ይህን አስመልክቶ ፀሐፊው እንዳለው
እሾህክ ብቻ ያለው ቅንአት ጋሬጣ ነው፤
*" የተንከል ጨጎጎት ልብሴን እንዳይነካ*
*ማለፍ አፈራለሁ የቅናትን ሜካ"*
የዚህ ሁሉ ችግር ጥፋት መሰረቱ
ያለ አቅም ምኞት ነው እንደ ጎረቤቱ።
የአንደኛው መነሳት አንዱን ደስ ይበለው
እንደዚህ ቢለምዱ ቅናት ቦታ የለው!
በግልም በህብረት በአገርም መሻሻል
ሰው ደስ ሊሰኝ በእውነት ይገባዋል።
ይህም ግንኙነት ያስተሳስረዋል
ተቸገርኩ እንኳን ቢል ፈቅዶ ይረዳዋል
እንደዚህ አባቶች ዘመናት ኖረዋል፤
ይህን በጎ ታሪክ ትውልድ ሆይ አደራ
እንዳያዘናጋህ ቅናት ባሳንጋራ።

## ◆ ደስታና ምስጋና

ቸገረኝ የማይል አመስጋኝ ለሁሉ
ደስታ የተሞላ ህይወቱን በሙሉ
ነበረ አንድ ሰው ምስጋና ባህሉ።
በሃብት ያለደረጀ እንደ ጎረቤቱ
ሁልጊዜ ደስተኛ አይከፋ ፊቱ
ፈጣሪን አመስጋኝ ስለ ጤንነቱ።
ይህን ሰው በማየት ሁሌ የሚገረም
አንድ ባለፀጋ ሰው ጎረቤቱ ነበር፤





በጣም ድሃ ሰው ነው ሃብት ንብረት የለው
ምን እያገኘ ነው እንዲያ የሚደሰተው
ይህ ሁሉ ንብረት እያለ በእጃችን
መንገድ አንታይም እንደ እርሱ ደስ ብሎን፤
የዚህ ደስታ ምንጩ ምስጢሩ ምን ይሆን
ብሎ ሲያስብ ኖረ ለመጠየቅ አፍሮ
ክብሩ እንዳይቀነስ እንዳይታይ አብሮ።
ጥያቄው በአእምሮው አሳጣው እረፍት
ልጆቹንም ላከ እንዲያጣሩለት፤
ከልጆቹ አንደኛው ባለመሰልቸት
በጣም አዘውትሮ ይመላለስ ጀመር
ምስጢሩን ለማግኘት ቀላልም አልነበር።
ድሃው ግራ ገብቶት አንድ ቀን ጠየቀው
በአለፉት ሳምንታት ሁሌ የምትመጣው
አዲስ ሆኖብኛል ቀደም ያለነበረ
ንገረኝ ምን ፈለግህ አለና ጨመረ።
ልጁም አጫወተው የተላከበትን
አጣራ መባሉን የድሃ ደስታ ምንጩን
ወላጆቼ ሃብታም ግን የላቸው ደስታ
አንተ ትኖራለክ ሁሌም በፈገግታ።
ደስ ለመሰኘት መሰረቱ ምንድን ነው
ከሃብታም ርቆ ድሃው ቤት የገባው!
በማለት ነገሩን አስረዳ ዘርዝሮ
ድሃውም መለስ አልሰጠው ቀጠሮ።
በደስታ የሚያኖረኝ በደስታ ዜማ
ውስጤን ብርሃን ሞልቶት የማላውቅ ጨለማ
የደስታ ምንጩ እግዜአብሔር ብቻ ነው
በደስታ ምስጋና ሰውን የሚያኖረው
የባለፀጋው ልጅ ጨዋታ ቀጠለ
ጤነኝነት ብቻውን ይበቃል ወይ አለ!
ሙሉ ጤነኛ ነኝ ውየ እገባለሁ
ጦም አድሬ አአውቅም ሰርቼ እበላለሁ፤
የሚያልመው ሁሉ ቆሞም ተቀምጦ
ለመታየት ብቻ ከሌሎች በልጦ
እንዲህ እየኖረ ምስጋና የራቀው
ብዙ አለ የሰው ልጅ ደስታ የሌለው።
ጤንነት ዋና ነው መሰረት ለሁሉ
የሌለ የለውም ገንዘብ የለ አትበሉ።
ልጁም ተመልሶ ሲያጫውት ለአባቱ
በጣም ተገረመ ተለወጠ ፊቱ፤
ማሰብም ጀመረ ስለወደፊቱ

ከዚያ ቀን ጀምሮ ደስታ ገባ ቤቱ
ደስታን አወቀ ደስታ የማያውቀው::
ጤና ስለሰጠው የማያመሰግን
በገንዘብ አይረካም ቢያገኝም ቢሊዮን
ሰው ገንዘብን ብቻ ከተመለከተ
እውነተኛ ደስታ በቃ አከተተ::

## ◆ የድሮ ሃብታም መለኪያ

ድሮ እንዲህ ይባል ነበረ
በአገሩ በሰፈሩ የተከበረ
በኑሮው በሃብቱ የጠነከረ
በላቡ በሥራው ያደረ
አደራ ቢሰጠው የታመነ
ባይሸመግልም በዕድሜው ጠና ያለ
ሲጠሩት አንቱ የተባለ
መልካም ስመጥር የሆነ
ቁመናው የሞላ የደነደነ
ኑሮው የሰከነ
ለዘመድ ለአዝማድ መመኪያ የሆነ
ለገጠር ለከተማው ምሣሌ የሆነ
በደስታና በድሎት
የመኖሩ ምልክት
ፊቱ የሚመስል ቅባት የተደፋበት
አምባሬ ጭቃ ያላሰነኩት
ሚዛን ላይ ቢወጣ
ኪሎ የሚመታ
በንብረቱ የከራ
አንቱ ተብሎ የሚጠራ
ግብር ሲያበላ የሚያጠግብ
ደብሩን ሁሉ የሚመግብ
በአካባቢው ነዋሪ የሚመረጥ
ቁርጥና ጠጅ የሚሰጥ
ለእንደራሴነት የሚበቃ
ወኪል የሚሆን ጠበቃ





ልዩ ምልክቱ የታወቀ
ሲያገለግል የሰነቀ
መታጠቂያውን ያጠበቀ
አስታራቂ የሚሆን ዳኛ
ይህ ነበረ አንዱ መመዘኛ
አንተም አንቺም ተው ብሎ ሲናገር
የሚፈሩት የሚከበር
ባለሥልጣንም የሚያከብረው
ሌባ የሚፈራው
በሃብቱ ምክንያት
ዕምነት የሚጥሉበት
ፍርድ ቤት ቢቆም የሚያሸንፍ
መቶ ሰው የሚያሰልፍ
ዋስ ሆኖ የሚያወጣ
ድራሽ የሚያጠፋ ሲቀጣ
በመንገድ ሲያልፍ የሚሰግዱለት
በጋብቻ ለመዛመድ የሚመኙት
ለምስክርነት ሲቀርብ የሚታመን
ባይሰራም በተሰፋ የሚመሰገን
ይህን ነበር ይመስል ነበር ድሮ
ብዙው ነገር ተቀየረ እንጂ ውሎ አድሮ።
በአሁኑ ዘመን ስለ ሃብት ሲነሳ
ስለ ሃብታም ሰውም ሲወሳ
አካባቢውን ለማሳመን ግብር ማብላት
ለመመረጥ በሬ ማረድ ጠጅ ጠላ ማጠጣት
ሁሉ ተቀየረ ይህን ማን አሰቦት።
ዛሬ ወጣት ሁሉ በሃብት ደነደነ
በሰላሳ ዓመት ዕድሜ ቢሊየነር ሆነ
ሰው በትምህርቱ፣ በሃብቱና በምላሱ ተማመነ
ማብላትና ማጠጣት ተቀየሮ ጉቦ አከለ
ሲሰለጥን ደግሞ ኮራፕሽን ተባለ።

## ♦ ዘ አሜሪካን ድሪም

ሃይ ስኩል እያለ ቱሪስት ሲገይድ
ፈረንጅ ያረፈበት ሆቴል ሲያሳድድ
ብሮክን እንግሊሽ ያለግራመሩ በራሱ ሲያስሄድ፣
መፍጨርጨር ጥሩ ነው ተማረ በግድ።
ዕድሜውም ጨምሮ እግሩ እንደረዘመ
ውጭ መሄድ አማረው ነበር የታለመ።
ምስራቅና ምዕራብ አውሮጳን ዞሮ
ተምሮና ሰርቶ እየኖረ ጠንክሮ
ግን መድረስ አልቻለም ከጠዋት ዓላማው
ድካም ብቻ ሆነ የዓመታት ጉዞው።
አልሳካ ቢለው ሁሉን በመሞከር
የአሜሪካው ስደት ሆነለት የማይቀር።
ወዳጅ ዘመዶቹ ሃሳቡ ገርሟቸው
ባለህበት አገር ምንም ሳይጎድልብህ
በተማርከው ሙያ ሰርተህ ትኖራለህ
አሜሪካ መሄድ ለምን እንዳማረህ
ምስጢሩ አልገባንም አስረዳን እባክህ
ብለው ሲጠይቁት ለማስረዳት ሞከረ
የአሜሪካን ድሪም በውስጡ ነበረ።
አሜሪካን ድሪም እላቸው ደጋግሞ
የበለጠ ተምሮ የተሻለ ሊኖር ነበርና አልሞ።





ቀድሞ ሳያስበው የአሜሪካን ስደት
ሰው አይቀርም ሲሉ ከአሜሪካና ሞት
እያለ ያስብ ነበር ምንድን ነው የሚቀልዱት
ቆይቶ ግን ገባው እሱም ሲገባበት።
ሕግና ስርዓቱን ደንቦቹን አክብሮ
ሰርቶ ለማደግ ሁሉን ጥሮ ግሮ
ኑሮውን ጀመረ ሳያማርጥ ሥራ
ስራ ስለሚገኝ ስራ እየተሰራ፣
በህክምና መስክ ስራውን ቀጥሎ
ለጉልበቱ ሳይጓጓ ሲታዘዝ ሁሉን እሺ ብሎ
ዓመታት አሳለፈ ክፋም ቢኖር ችሎ።
ወዲያው እንደተቀጠረ ምን ተማርክ ሲሉት
ነገራቸው እና የማይጎዳው መስሎት
በኋላ ሠራተኞች ሲሰቁ ሲቀልዱበት
መናገሩን ጠላው አሁን ቀረቀረው
እንዴ ከአፍ የወጣን ማንስ ይመልሰው።
የተማረው ሌላ የሚሠራው ሌላ
በእነርሱ አይፈረድ ጊዜ ሰው አዳላ።
ለእርሱ መልካም ሆኖ ለሌላውም ባይጥም
ከግቡ ለመድረስ ሥራ አላማረጠም።
ሆስፒታል ተቀጥሮ በርትቶ እየሰራ
ወደ አለቃው ቢሮ አንድ ቀን ተጠራ።
ምን ጥፋት ሰራኩኝ ብሎ እየሰጋ

የቢሮውን መዝጊያ አንኳኳና ገባ፣
ሰላም አለውና እንዲቀመጥ ጋበዘው፣
ስቦ ተቀመጠ አለው እና ታንኪው።
ዓይኑ ሲቁለጨለጭ ስላልገባው ጥሪው፣
ግራ እንደተጋባ አለቃው አየና
ቀኝ እጁን ዘርግቶ ኮንግራጁሌሰንስ አለው ተነሳና፣
ምን አኘሁ ብሎ ሊጠይቅ ሲቃጣው
የዓመቱ ታታሪ ሠራተኛ ተመርጠሃል አለው።
እንዲዘጋጅ ነግሮት ለሽልማቱ ቀን
ደስ ብሎት ወጣ ወሰዶት ፍርሃቱን፣
ሰንት ሰራተኛ የአገሬው ባለበት።
እግዚአብሔር ይመስገን ለመመረጥ መብቃት
ሥራውን ቀጥሎ እንዳለፈ አንድ ዓመት
አደጋ ገጠመው ተቀረጠ ጅማት
ፊዚካል ሜዲካል ሁሉንም ሞከረው
ሊሆን ግን አልቻለም እንደ መጀምሪያው
ሐኪሙም አዘዘ ው ሸክም ከለከለው
ጭራሽ ይህ እጅህን እንዳታጣ አለው።
የሐኪሙን ትዕዛዝ ለአለቃው አሳይቶ
ሥራ ቀይሩኝ አለ ተስፋ አድርጎ ተዝናንቶ።
አለቃውም አንብቦ ፊቱን አኮሳተረ
ምን ዓይነት ቀላል ሥራ? አለና ጨመረ።
ድጋፍ የሚጠይቅ ቀውጢ ቀን ሲመጣ





ኮከብ ሠራተኛው አሁን ዋጋ አጣ
አሠራለሁ የሚል በጤናው ሲመካ
አሁን ለውጡ ገባው ዚስ ኢዝ አሜሪካ።
ለቀላል ሥራዎች ዕውቀት ቢኖረውም
ከገባበት ሌላ ዕድል አልሰጡትም።
ሕጉ ለእርሱ አልሠራም ሕጉ አልደገፈውም
እናም የግድ ሆነ ሙያውን መቀየር
አንድ በር ሲዘጋ መፈለግ ሌላ በር።
ራሱን ያዘጋጀ ያገኘውን ለመሥራት
መፍትሄ አይጠፋም ከአደረገ ጥረት
እየሠራ ይኖራል እግዚአብሔር ይመስገን
በጤንነት እና በአቅም ሰላስቻለው ሁሉን
በአዕምሮው እያሰበ ከታች የቀሩትን
ወደ ላይ ለማደግ እየጣረ የአቅሙን
ጠንክሮ እየሠራ አቅሙ የቻለውን
ውጤት ተስፋ ኣድርጎ ይጠብቃል ነገን።
አሁንም ይኖራል ሁሉን ጥሮ ግሮ
በአሜሪካ ድሪም ነገን ሲያይ አሻግሮ።

## ♦ የታርካብ ምስጢር

ከመምዘዝ የሰውን ሥራ ከመጠምዘዝ
ታሪክ ሲሠራ አብሮ በማገዝ
ርቀት ያለው መንገድ መ□ዝ።
ካጂነት ሳይኖር ተማምኖ
ብችኝነን ነጥሎ አንድ ሆኖ

ብዙአየሁ አበጀ

# ታ ር ካ ብ

## ከትዝብት ማሕደር



ብዙአየሁ አበጀ

ከመጽሐፉ የተወሰደ

ሙሪት ከድህነቷ ይሁን ከስስታምነቷ የተነሳ አላውቅም፡ ብቻ የደረቀ ማካሮኒ ጊዜው ያለፈበት ይጥፍር ቀለም ቀብታ መዓዛው ተመጦ ባለቀ ማስቲካ እያጣበቀች ነው የጆሮ ጉትቻ ስትጠቀም የማውቃት" አለች። እኔም በንግግሯ ተገርሜ፡ ምንድን ነው የምታወሪው ስላት . . . . :